# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 83ኛ ዓመት ቁጥር 048 ጥቅምት 18 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!








# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የንኢሴ ፓልም ስፕሪንግ ሉጅ ፕሮጀክትን አስጀመሩ

## - በአፋር ክልል የበጋ ስንዴ ምርት ሥራ ተጀምሯል

ገጽ 8

ፎቶ፡- በሪሁን ታደሠ



መስፍን ዓርአያ (ፕ/ር)

## ሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳካ መገናኛ ብዙሃን ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል

ጌትነት ምህረቴ

አዳማ፡- በኢትዮጵያ ሊካሄድ የታቀደው ሀገራዊ ምክክር እንዲሳካ መገናኛ ብዙሃን ትክክለኛ መረጃዎችን በወቅቱ በማድረስ ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ተገለጸ። "የሚዲያ ሚና ለሀገራዊ ምክክርና መግባባት"

ሀገራዊ ምክክሩ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## "የአዳዲስ ክልሎች መመሥረት ለሕዝቦች የዘመናት ጥያቄ ምላሽ የሰጠ ነው"

- አቶ አደም ፋራህ
የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት



ልጅዓለም ፍቅሬ

ሆሳዕና፡- የአዳዲስ ክልሎች መመሥረት ለሕዝቦች የዘመናት ጥያቄ ምላሽ የሰጠ መሆኑን የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ተናገሩ።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ይፋዊ ምሥረታና ክልሉን የማስተዋወቂያ መርሃ-ግብር ትናንት በሆሳዕና ከተማ ተካሂዷል።

"የአዳዲስ ክልሎች ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## ‹‹የክልሉን ጸጥታ ለማስጠበቅ ከሚከናወኑ ተግባራት ጎን ለጎን የልማት ሥራዎችም በአግባቡ እየተሠሩ ነው››

- መንገሻ ፈንታው(ዶ/ር)
የአማራ ክልል መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ



ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- የክልሉን ጸጥታ ለማስጠበቅ ከሚከናወኑ ተግባራት ጎን ለጎን የልማት ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ እየተሠሩ መሆኑን የአማራ ክልል መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ። የቢሮው ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር)

‹‹የክልሉን ጸጥታ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል


eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

Medhin Decor
የተንጣለለ ድንቅ የሰርግ አዳራሽ ከነ ሙሉ የውበት ስራ
የተሟላ የምግብ ዝግጅት ከሙሉ መስተንግዶ ጋር
ለሠርግ ለልደት እንዲሁም ለልዩ ልዩ ዝግጅቶች
አድራሻ 1ኛ በሌ ጌቱ ኮሜርሻል ጀርባ
2ኛ ከቃሊቲ ማሰልጠኛ አለፍ ብሎ ቆርኪና ጣሳ ፋብሪካ ገባ ብሎ
Contact Us 0911222993/ 0911208918

ቴክኖ ፋይበር
Technofiber
09 41 41 48
የምንሰጣቸው አገልግሎት
• ማንኛውንም በፋይበር ግላስ የሚሰሩ ነገሮችን በደንበኞች ትእዛዝ እናመርታለን
• የፋይበር ግላስ ጥሬ እቃዎችን አስመጥተን በጅምላም ሆነ በችርቻሮ እናከፋፍላለን
• ለፋይበር ሥራ የሚሆኑ የተለያዩ ፍሬም ፣ የታንከር እንዲሁም የተለያዩ ምልዶችን እንሸጣለን
• በተጨማሪም በዚህ ሥራ መሰማራት ለሚፈልጉ ውስን ወጣቶች የነፃ ሥልጠና እንሰጣለን
+251 940526393/+251948969696

AfriSky PLC ETHIOPIA
REBAR | WIREROAD | RHS | TANKER | NAIL
0940 80 80 80 | 0940 90 90 90 | 0911 21 72 55 | 0940 50 50 50

AMG STEEL FACTORY
ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory

ዜና

# ከ15 ሺህ በላይ ወጣቶች በሥራ ላይ ልምምድ ፕሮግራም ተጠቃሚ ይሆናሉ

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- በ2016 ዓ.ም በሚከናወነው ሁለተኛው ዙር የወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ ፕሮግራም በመዲናዋ የሚገኙ ከ15 ሺህ 341 ወጣቶች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

ቢሮው "ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ፕሮግራም" በሚል ሃሳብ ከአምራች ኢንዱስትሪ ባለቤቶች ጋር ትናንትና ውይይት አካሂዷል።

በወቅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የቢሮው ኃላፊ አቶ ጃንጥራር አባይ እንደገለፁት ፤ በሁለተኛው ዙር ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ፕሮግራም በዘንድሮው ዓመት ከ15 ሺህ 341 ወጣቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ፕሮግራሙ ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 25 የሚገኙና ከ12 ክፍል በታች የሆኑ ወጣቶች በተለያዩ የግል ድርጅቶች ገብተው የስድስት ወራት የሥራ ላይ ልምምድ እንዲያገኙ የሚረዳ መሆኑን አስታውቀዋል።

በዓለም ባንክና በኢትዮጵያ መንግሥት ትብብር ለአምስት ዓመታት የሚቆየው ፕሮግራሙ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ከተሞች የሚገኙ 70 ሺህ ወጣቶች ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

ከአጠቃላይ ተጠቃሚዎች መካከል 70 በመቶዎቹ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ወጣቶች መሆናቸውን ገልጸው፤ ባለፈው ዓመትና ዘንድሮ የሥራ ላይ ልምምድ ያገኙትን ጨምሮ በአጠቃላይ አምስት ዓመታት ውስጥ 49 ሺህ የመዲናዋ ወጣቶች የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ አስረድተዋል።



አቶ ጃንጥራር አባይ

ወጣቶችን በተለያዩ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ገብተው የተግባር ልምምድ እንዲያገኙ በማድረግ እራሳቸውን ለቅጥር እንዲያዘጋጁና የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ጥረት እንደሚደረግ አመላክተዋል።

ወጣቶች በሥራ ላይ ልምምዱ የሚያስፈላጓቸውን የሥራ ክህሎቶች በበቂ ሁኔታ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ያግዛል ሲሉ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የሥራ ስምሪት ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ ሰበህዲን ሱልጣን በበኩላቸው፤ ፕሮግራሙ የወጣቶችን ክህሎት በማሳደግ ረገድ አዎንታዊ ለውጥ እንደሚኖረው ጠቁመዋል።

በመጀመሪያው ዙር በብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ፕሮግራም ትግበራ 10 ሺህ 500 ወጣቶችን የሥራ ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ የሚያችል እንቅስቃሴ በማድረግ አምስት ሺህ 193 ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤ ከነዚህም መካከል አንድ ሺህ 206 ወጣቶች ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል ብለዋል፡፡

ሁለተኛውን ዙር የፕሮግራሙ ትግበራ የሚሳተፉ 15 ሺህ 341 ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግና ተቀብሎ ለማሠልጠን አራት ሺህ የተግባር ላይ ልምምድ የሚሰጡ ድርጅቶች እንደሚያስፈልጉ አስታውቀዋል።

በከተማው የሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች በርካታ ወጣቶችን ተቀብለው ማሠልጠን የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

ወጣቶቹ የተግባር ልምምዱን በሚያገኙባቸው ስድስት ወራት ለእያንዳንዳቸው 14 ሺህ 520 ብር የሚሰጣቸው ሲሆን፤ ተጨማሪ ሥራ ማፈላለጊያ የሚሆን ሰባት ሺህ 260 ብር እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል።

ህጻን ልጅ ላላቸው ሠልጣኝ እናቶች ደግሞ በየወሩ ተጨማሪ 945 ብር እንደሚሰጣቸው ተናግረዋል።

ለጠቅላላ የፕሮግራሙ የሚውለው የአንድ ቢሊዮን ብር ድጋፍ በዓለም ባንክና በኢትዮጵያ መንግሥት የሚሸፈን መሆኑን አስታውቀዋል፡፡



ኢንጂነር ሃብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር)

## በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚፈጠሩ ጉዳቶችን ለመከላከል በቂና ወቅታዊ መረጃ ያስፈልጋል

ዳግማዊት አበበ

አዳማ፡- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚፈጠሩ ጉዳቶችን ለመከላከል በቂና ወቅታዊ መረጃ እንደሚያስፈልግ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ገለጸ።

የአየር ጠባይ አገልግሎት ማዕቀፍን ለማፅደቅና ወደ ክልሎች በማውረድ ተፈፃሚ ለማድረግ ያለመ የክልሎችና የባለድርሻ አካላት መድረክ በአዳማ ተካሂዷል።

መድረኩን በንግግር የከፈቱት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) እንዳስታወቁት፤ በአየር ንብረት ለውጥ ችግር ምክንያት ዓለም ከፍተኛ ስጋት ውስጥ በመሆኗ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚፈጠሩ ጉዳቶችን ለመከላከል በቂና ጊዜውን የጠበቀ መረጃ ማቅረብ ወሳኝነት አለው።

የአየር ንብረት ለውጥ ሊያስከትል የሚችለውን ተፅዕኖ በዘላቂነት ለመቋቋም የሚያስችል ብሔራዊ የአየር ጠባይ አገልግሎት ማዕቀፍን በየደረጃው ባሉ መዋቅሮች በአግባቡ መተግበር እንደሚገባም አሳስበዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ አደጋን ለመከላከል መረጃን በተገቢ ሁኔታ ማጠናቀርና መተንተን እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ አስቀድሞ የአየር ንብረት ለውጥን መረጃ አለመሰብሰብና በመረጃው አለመጠቀም የተፈጥሮ ውሃ ሀብትን በመጉዳት ዜጎችን ለከፋ ችግር እንደሚዳርግ አስገንዝበዋል።

በሀገራችን የሚስተዋለውን የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳት ለመቀነስም የሚመለከታቸው ተቋማት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ጠቁመው፤ አሁን ላይ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በዘርፉ ሳይንሳዊ መረጃ በማቅረብ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ በበኩላቸው፤ ኢንስቲትዩቱ ኢትዮጵያ የሚያጋጥማትን የአየር ጠባይ ሁኔታን በመተንበይ መረጃ እያቀረበ መሆኑን ገልጸው፤ መረጃውን የሚመለከታቸው አካላት ጥቅም ላይ ሊያውሉ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቷን የአየር ሁኔታ መረጃዎችንም በክልል ደረጃ ወርዶ በመሥራት የጥንቃቄ ርምጃዎች እንዲጠናከሩ የበኩሉን ሚና እየተወጣ መሆኑን አመላክተዋል።

የውይይት መድረኩ በኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የተዘጋጀ ሲሆን፤ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ዜጎች ላይ የሚደርሰውን አደጋ አስቀድሞ መከላከል የሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት መሆኑን ተሳታፊዎች አንስተዋል።

## የአምራች ኢንዱስትሪውን የግብዓትና የመሠረተ ልማት ተግዳሮት ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን እየፈተኑ የሚገኙ የግብዓት አቅርቦትና የመሠረተ ልማት ተግዳሮቶችን ለመፍታት የሚያስችል ጥረት እያደረገ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለጸ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በዘርፉ ስለሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችንና መፍትሄዎች በተመለከተ ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተዋናዮች ጋር ውይይት አካሂዷል፡፡

በወቅቱ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሀሰን ሙሐመድ፤ አምራች ኢንዱስትሪውን እየፈተኑት ያሉ የግብዓት አቅርቦትና የመሠረተ ልማት ግንባታ ተግዳሮቶች በርካታ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪውን ለማሳደግና የሀገርን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እውን ለማድረግ የሚያስችል ሥራ በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በግብዓት እጥረት በኩል እየገጠሙ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የገበያ ትስስር፣ የኢንዱስትሪ ለኢንዱስትሪ ግንኙነት፣ የብድርና የፋይናንስ አቅርቦት ላይ ትኩረት ያደረጉ ሥራዎች ከተለያዩ ተቋማት ጋር በትብብር እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

ከአርሶ አደሩ የሚገኘውንና የግብርና ምርት ብክነት ሳይደርስበት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ተደራሽ ለማድረግ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓት ድርጅት ከብሔራዊ ልማት ባንክ ባገኘው ሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በስፋት እየሠራበት መሆኑን አስታውቀዋል።

ሀገሪቱ እያስመዘገበች ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት አፅንቶ ለማስቀጠል አምራች ኢንዱስትሪው ትልቅ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ጠቁመው፤ ዘርፉ ያሉበትን ማነቆዎች በጋራ በመፍታት ለሀገር ዕድገት በጋራ መሥራት እንደሚገባ አመላክተዋል።



አቶ ሀሰን ሙሐመድ

አምራች ኢንዱስትሪው የሀገርን የኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ከመፍታት በተጨማሪ ተተኪ ምርቶችን እያስፋፋ ነው፤ በተያዘውም ዓመት 96 ተተኪ ምርቶች ለማምረት ታቅዶ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በአምራች ኢንዱስትሪው የገጠሙትን የግብዓትና የመሠረተ ልማት ችግሮችን በመፍታት ሀገርን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር መለወጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ በመሆኑ እየተሠራበት እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በአምራች ኢንዱስትሪው የሚገጥሙ ተግዳሮቶች በመፍታት ሀገርን ምርትና ምርታማነት የማሳደግ ሥራ ተጠናክሮም ይቀጥላል ሲሉ አመላክተዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ የሆኑት በፕሮፌሰር ሽመልስ አድማሱ በመርሀ-ግብሩ ላይ አምራች ኢንዱስትሪው እየገጠመ ያለውን ችግርና መፍትሔ በተመለከተ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

በጥናታቸውም አምራች ኢንዱስትሪው ዘርፈ ብዙ የሆኑ ማነቆዎች እንዳሉበትና ዋና ዋናዎቹም የግብዓትና የመሠረተ ልማት ችግሮች ናቸው ብለዋል፡፡

የሀገርን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማስቀጠል ከውጭ ምርትን የማስገባትና ጥሬ ዕቃ የመላክ ጉዳይ መቆም አለበት ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ ያለንን ጥሬ ዕቃ በሀገር ወስጥ በማምረት የውጭ ምቶችን መተካት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪውን ችግር መፍታት ሀገሪቱ በምግብ ራሷን እንድትችልና የምግብ ደህንነትን እንድታረጋግጥ ያደርጋል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ሀገርን ሁለተናዊ ዕድገት ለማስቀጠል በየዘርፉ የሚገጥሙ ችግሮችን በጥናት የመለየትና የመፍታት ሥራ ሊሠራ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የግብርናው ዘርፍ ዕቅድም ውጤትም ያማረ ነው!

በተያዘው 2016/17 የምርት ዘመን በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ብቻ 117 ሚሊየን ኩንታል የስንዴ ምርት እንደሚጠበቅ የግብርና ሚኒስቴር ሰሞኑን አስታውቋል። ልማቱ በሦስት ሚሊየን ሄክታር መሬት ላይ የሚካሄድ ሲሆን፣ ለምርት ዘመኑ የሚያስፈልጉ እንደ ግብአት አቅርቦትና የማሳ ዝግጅት ያሉ ስራዎች በሁሉም ክልሎች እየተፈጸሙ መሆናቸውንም ሚኒስቴሩ አስታውቋል፡፡ በቅርብ ጊዜ የወጡ ዘገባዎች እንዳመለከቱትም፤ ክልሎች በዘንድሮው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ዕቅዳቸውንና ዝግጁነታቸውን እያረጋገጡ ናቸው፡፡

አሁን የበጋው ወር እንደመያዙ የተጠቀሱት መረጃዎች ወቅታዊ ናቸው፡፡ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ላይ በስፋት መሥራትና መነገር በሚጀመርበት በዚህ ወቅት ይህን ዜና መስማት ሥራው በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ በክልሎችም በፌዴራል መንግስት ደረጃም እየተደረጉ ያሉ ዝግጅቶች ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የተሰጠውን ትኩረት በሚገባ ያመላክታሉ፡፡

እንደሚታወቀው በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የሚሸፈነው ማሳና የሚገኘው ምርት መጠን በየዓመቱ እየጨመረ መጥቷል፡፡ መረጃዎች እንደጠቆሙት፤ የመስኖ ልማቱ ከሦስት ዓመት በፊት በቆላማ አካባቢዎች የተጀመረው በ117 ሺ ሄክታር መሬት ላይ ሲሆን፣ በወቅቱ የተገኘው ምርትም 3 ነጥብ 6 ሚሊየን ኩንታል ነበር፡፡ በቀጣዩ ዓመት 24 ነጥብ 5 ሚሊየን ተመርቷል፤ ባለፈው ዓመት 53 ሚሊየን ኩንታል ለማግኘት ታቅዶ 47 ሚሊየን ኩንታል አካባቢ ተገኝቷል፡፡

ዘንድሮ በመስኖ ልማቱ የሚሸፈነው መሬትም የሚጠበቀው ምርትም በእጅጉ የላቀ ነው፡፡ በልማቱ ለማግኘት የታቀደው 117 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ባለፈው ዓመት በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ ከተገኘው ምርት ከእጥፍ በላይ ይሆናል፡፡ በዚህ ዓመት ለማግኘት የታቀደው የምርት መጠን ባለፈው ዓመት በመኸርና በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት አንደሚገኝ ይጠበቅ ከነበረው 107 ሚሊዮን ኩንታልም ይበልጣል፡፡

የሚታረሰው የመሬት መጠንም እንዲሁ ከአምናው አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊየን ሄክታር ከእጥፍ በላይ ጨምሮ ሶስት ሚሊዮን ደርሷል፡፡ ዘንድሮ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ የሚታረሰው መጠን በቀደሙት ዓመታት በመኸር ወቅት በስንዴ ይለማ ከነበረው መሬት የሚበልጥበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

እነዚህ ሁሉ መረጃዎች በራሳቸው ብቻ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ ግዙፍ ዕቅድ መያዙን ያመለክታሉ፡፡ እየተደረገ ያለው ዝግጅትም ዕቅዱን ለማሳካት ይመጥናል ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ሥራው እየሰፋ ዝግጁነቱም እየላቀ እንደመጣ ሁሉ፣ ክትትልና ድጋፉም በዚያው ልክ የተጠናከረ ሊሆን ይገባል፡፡

ዝግጁነቱ፣ ክትትልና ድጋፉ በሁሉም የልማቱ ምዕራፎች ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ ይህ ሲሆን የሚጠበቀውን ማሳ በዘር መሸፈን፣ የሚጠበቀውን መጠን ምርትም በእርግጠኝነት ማግኘት ይቻላል፡፡

የፌዴራል መንግስት ባለፉት ዓመታት በማዳበሪያ አቅርቦቶች ላይ የታዩ ችግሮችን ለመፍታት የማዳበሪያ አቅርቦቱን ከአሁኑ መጀመሩ ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱም የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ዘንድሮ የተያዘው ዕቅድ ሰፊ ነው፤ ይህም ግብአት በስፋት ማቅረብንም ይጠይቃል፡፡ ማዳበሪያ አስቀድሞ መግዛቱና መጓጓዝ መጀመሩ ለተያዘው ሰፊ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት መልካም አጋጣሚ ተደርጎ ሊታይ ይገባዋል፡፡ ለምርት ዘመኑ ከተገዛው ማዳበሪያ የተወሰነው በዚህ ወር መጨረሻ ጅቡቲ ወደብ የሚደርስ መሆኑም ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱም የበለጠ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

ምርትና ምርታማነት ለመጨመር ማሳ ማስፋፋት አንዱ መንገድ ነው፤ ብቸኛው መንገድ ግን አይደለም፡፡ በስንዴ ዘር የሚሸፈነው ማሳ መጨመሩ ከዚህም ለማግኘት የታቀደው ከፍተኛ መሆኑ አንድ ነገር ሆኖ በሄክታር የሚገኘው ምርታማነት መጨመር ላይም በትኩረት መሰራት ይኖርበታል፡፡ የበጋ መስኖ ሲጀመር በሄክታር 35 የነበረው ምርታማነት በፈረንጆቹ 2022 ወደ 40 ኩንታል አድጎ እንደነበርም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህ የምርታማነት ዕድገት እንዲመጣ መሥራት የዘንድሮው ዐብይ ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡

በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ ባለፉት ዓመታት የተገኙ ስኬታማ ተሞክሮዎች እቅዱን ለማሳካት ጥሩ አቅም ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ በስንዴ ልማቱ ሀገርንም መንግስትንም በስኬት ያስጠራ ተግባር በዓመታቱ ማከናወን መቻሉ ይታወቃል፡፡ ሀገሪቱን ለሌሎች ልማቶቿ ልታውለው ከሚገባት ውስን የውጭ ምንዛሬ ላይ አንስታ ስንዴ ትገዛ ከነበረበት ሁኔታ ማውጣት ተችሏል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፤ ከሀገራዊ ፍጆታዋ የተረፉትን ስንዴ ወደ ጎረቤት ሀገሮች በመላክም የውጭ ምንዛሪም አግኝታለች፡፡ ከሁሉም ከሁሉም ከስንዴ እርዳታ ጥገኝነት መላቀቅ ተችሏል፤ በስንዴ ምርት ሉአላዊነት ተጠብቋል፡፡

ዘንድሮም ይህን ታሪክ በሚገባ መድገም የሚያስችል ዕቅድና ዝግጁነት ተይዞ ወደ ልማቱ ተገብቷል ማለት ይቻላል፤ የግብርና ሚኒስቴርም የክልሎችም ዝግጅት ይህን ያመለክታል፡፡ የተጀመረው ርብርብ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሌሎች ባለድርሻ አካላትም አጋርነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

በተለይ የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴርና በክልል የሚገኙ ተመሳሳይ ተቋማት ለመስኖ ስራ የሚያስፈለገውን ውሃ መሰረተ ልማት በመዘርጋት፣ እክል ሲገጥም በመጠገንና በመሳሰሉት ምክር በመስጠት ኃላፊነታቸውንም አጋርነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዕቅዱ ስፋት አኳያ የመላው ሕዝብና ሌሎች የልማት ኃይሎች ድጋፍም ወሳኝ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኢትዮጵያን የሚወክል የአትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድን ሊኖር ይገባል!

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በበጎ ከታወቀችባቸው ጉዳዮች መካከል አትሌቲክስ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። ይህ ስፖርት የሀገርን ገጽታ ከመገንባት ባለፈ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይም ከፍተኛ ሚናም አለው። ቀደም ባለው ጊዜ በጥቂት አትሌቶች ባንዲራዋ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያስቻለ ድል ሲመዘገብ ቆይቷል።

በሂደትም የአትሌቶችን ቁጥር መጨመር ተከትሎ የአሰልጣኞች፣ የውድድሮች፣ የክለቦች እና የማናጀሮች ቁጥርም አድጓል። በዚህም በዓለም አቀፍ ውድድሮች ውጤታማ የሆኑ አትሌቶች ኢትዮጵያን በክብር እያስጠሩ እዚህ ደርሰዋል።

ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብሄራዊ ቡድን ውስጥ ቀድሞ ይታይ የነበረው ስሜት እየተሸረሸረ፤ በተለያዩ ውድድሮች ላይም የውጤት እጦት ቀውስ እና በኢትዮጵያውያን አትሌቶችም ያልተለመደ እጅ መስጠት እየተስተዋለ ነው። በተመሳሳይ አትሌቶች ወጥ ባልሆነ አሰለጣጠን በማለፋቸው እንዲሁም በተለያዩና በግል አሰልጣኞች መሰልጠናቸው ባልተቀናጀ የአሯሯጥ ስልቶች የተቃኙት እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። በመሆኑም ሀገር የምትወከልባቸው ውድድሮች ሲካሄዱ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሚታወቁበት የቡድን ስሜት እየተመናመነ መምጣቱ ታይቷል።

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሚታወቁበት የመረዳዳት እና በቡድን የመስራት ልማድ በአንዳንድ ርቀቶችና አትሌቶች ዘንድ ይታይ እንጂ፤ በአመዛኙ እየቀረ መሆኑን በቅርብ የተካሄዱ ውድድሮች ምስክሮች ናቸው። በአንድ ብሄራዊ ቡድን እና ርቀት እየተሳተፉ በተለያየ የአሯሯጥ ስልት እርስ በእርስ በሚያደርጉት ፉክክርም ሀገር ዋጋ መክፈሏ በተደጋጋሚ ታይቷል።

ግለሰብ ሳይሆን ሀገር በምትወከልባቸው በእነዚህ የውድድር መድረኮች የኢትዮጵያን መለያ እና ባንዲራ ይዘው እየተሳተፉ ተፎካካሪን አዳክሞ ውጤት ከማስመዝገብ ይልቅ፤ እርስ በእርስ በሚደረግ ውድድር ክፍተቶች ተፈጥረዋል። ተቀናቃኝ ቡድኖችም ይህንኑ ክፍተት ተጠቅመው ውጤታማ ሆነዋል። በዚህ የኢትዮጵያውያኖች ስሜት መዳከም ምክንያትም ከጎረቤት ኬንያ እና ኡጋንዳ አትሌቶች ባለፈ አውሮፓውያን አትሌቶች ጭምር ምን ያህል እንደተጠቀሙ በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል።

የቀደመው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ውጤታማ ዘመን ሲታወስ የሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ እና ገብረእግዚአብሄር ገብረማርያም፣ ቀነኒሳ በቀለ እና ስለሺ ስህን፣ ደራርቱ ቱሉ እና ጌጤ ዋሚ፣... በመም ላይ የነበራቸው መናበብና ጥምረት አስደናቂ እንደነበር ከስፖርት ወዳጆች ሕሊና በቀላሉ አይሰረዝም። እርስ በእርስ ባላቸው መከባበር፣ መተባበር እንዲሁም ከአሰልጣኞቻቸው የሚሰጣቸውን መመሪያ ወደ ተግባር በመለወጥ ረገድ አስደናቂ ብቃት ነበራቸው። በዚህ ዘዴም በመላው ዓለም የናኘ እና እስካሁንም ከከፍታው ዝቅ ሊል ያልቻለ ዝናን መገንባት ችለዋል።

በእርግጥ አሁንም ይኸው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስኬታማነት ምስጢር የሆነው የቡድን ስራ በትልልቅ ቻምፒዮናዎች ላይ እንደሚፈለገው ባይሆንም መታየቱ አልቀረም። ለአብነት ያህል በቅርቡ በተካሄደው የቡዳፔስቱ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የሴቶች 10ሺ ሜትር ውድድር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ተከታትለው በመግባት የአረንጓዴውን ጎርፍ ታሪክ የደገሙበት ሁነት በቡድን ስራ የተገኘ ነው።

በሌሎች ርቀቶችም በቡድን ለመስራት ጥረት የተደረገ ቢሆንም ስኬታማ ባለመሆኑ ከሽፏል። ሩጫን የሚያውቁ የአትሌቲክስ ባለሙያዎች ለዚህ ምክንያት ነው የሚሉት የቡድን ስራ ራሱን የቻለ ችሎታ የሚፈልገው መሆኑን ነው። ሌላኛው ደግሞ የአሯሯጥ ስልቱን የሚነድፉት ባለሙያዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው በቀላሉ ሊተገበር የማይችል እንደሆነ ነው።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ቋሚ የአትሌቲክስ ብሄራዊ ቡድን የላትም። ኦሊምፒክ፣ የዓለም ቻምፒዮና እና መሰል ዓለም አቀፍ ውድድሮች ሲካሄዱም ጊዚያዊ ብሄራዊ ቡድን የሚቋቋም ሲሆን፤ አሰልጣኞችም ባስመረጧቸው አትሌቶች መጠን ይመረጣሉ። ታዲያ የዝግጅቱ ወቅት አልፎ ወደ ውድድር ሲገባ እንደ አንድ ሃገር ሳይሆን እንደ ግል ውድድር አንዱ አትሌት ሌላኛውን ለመርታት የሚያስችለው የአሯሯጥ መመሪያ የሚሰጠው በመሆኑ በውድድሩ ወቅት አለመግባባት ይፈጠራል። ይህን የእርስ በእርስ ፉክክር ከተቀናቃኝነትም አልፎ አለመግባባቶች ሲፈጠሩና በይፋ እስከመተናነቅ የሚደርስ መሆኑንም በተለያዩ መድረኮች ለመታዘብ ችለናል።

ከዚህ ባለፈ አትሌቲክስ የብቃት ጉዳይ መሆኑ ቀርቶ የቤተዘመድ አሰራር የተንሰራፋበትም ሆኗል። ታዋቂ የሚባሉና ስኬታማ አትሌቶችን ማፍራት የቻሉ አሰልጣኞች ወንድሞቻቸውን፣ ልጆቻቸውን እንዲሁም የቤተሰብ አባላቶቻቸውን በአሰልጣኝነት ስም ቀድመው በስራቸው ሳይታወቁ በድንገት ብሄራዊ ቡድኖችን እንዲመሩና ሌሎች የለፉበትን እንዲቀራመቱ እያደረጉ ይገኛሉ። በተመሳሳይ ሴት አትሌቶች በባሎቻቸው መሰልጠንን የሚመርጡ በመሆኑ አግባብነት የሌለውና በቡድን ውስጥም የስነምግባር መጓደል እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። ይህም አደጋውን የሚያንረው ሲሆን ብዙዎች ባልተጠበቀ መልኩ ያለ እድሜያቸው በጉዳትና በተለያዩ ምክንያቶች ከውድድር ውጪ መሆናቸውም የአደባባይ ምስጢር ነው። ይህ በዚህ ከቀጠለም በልምድም ሆነ በትምህርት ዝግጅት ባልተገኘ ስልጠና በርካታ መመሰቃቀሎች እንደሚደርሱም ግልጽ ነው።

በመሆኑም በእነ አበበ ቢቂላ፣ ዋሚ ቢራቱ፣ ምሩጽ ይፍጠር፣ ማሞ ወልዴ፣... ተገንብቶ ለዘመናት የኖረውን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ፤ ከጊዜ በኋላ የገጠመውን ስብራት የሚጠግን ወጌሻ አስፈላጊ ነው። ይኸውም ወጌሻ ከዚህ ቀደም እንደነበረው ቋሚ የሆነ ብሄራዊ ቡድን በመገንባት ውድድሮች ሲደርሱ ከመሯሯጥ እንዲሁም በተለያየ መንገድ የተቃኙ አትሌቶችን ወደ አንድ መንገድ ለማምጣት ከሚደረገው አላስፈላጊ ጥረት የሚያድን ይሆናል። በእርግጥም እነ ዶክተር ወልደመስቀል ኮስትሬ የገነቡትን ብሄራዊ ቡድን ፍሬ ዞር ብሎ ማየት መፍትሄው ይህ ብቻ መሆኑን ያመላክታል።

ከዓመታት በፊት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ለውጤት ማጣትና የቡድን ስሜት መጥፋት ምክንያቱ ይህ መሆኑን በማመን ብሄራዊ ቡድን ለማቋቋም በእንቅስቃሴ ላይ ነበር። ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሳካ በመቅረቱ አሁንም ድረስ ተግባራዊ ስላልሆነ ውጤትና ኢትዮጵያ እየተራራቁ ሕዝቡም ልቡ እየቆሰለ ቀጥሏል። በመሆኑም ፌዴሬሽኑ አስፈላጊውን ነገር በማድረግ ብሄራዊ ቡድን በማቋቋም በተመሳሳይ ስልጠና ሀገርን ብቻ ብለው የሚወዳደሩ አትሌቶችን መፍጠር ይገባዋል።

አሁን ላይ በኢትዮጵያውያን አትሌቶችና በጎረቤት ሀገራት አትሌቶች መካከል ያለው የብቃት ደረጃ እየተለያየ እንደመሆኑ ጠንካራ ስራ ይፈልጋል። ጊዜው በሄደ ቁጥር ሁኔታዎችም መለወጣቸው አይቀርምና በሁለቱም ርቀቶች ከ15 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ የነበሩ ክብሮችን አጥተናል። ይህ የሆነው በሂደት ነገሮች ዘመናዊ መልክ እየያዙ እና ጠንካራ አትሌቶችም እየተፈጠሩ ስለመጡ ነው። በመሆኑም የተወሰደብንን ክብር ወደ ሀገሩ ሊያስመልስ የሚችል ብቃት ላይ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ አትሌት ማፍራት የግድ ነው።

ስለዚህም ቋሚ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ብሄራዊ ቡድንን በመመስረት የተበተነውንና ባለመግባባት እየባከነ የሚገኘውን የአትሌቶች ብቃት መሰብሰብ ያሻል። ይህንንም ሃሳብ ፌዴሬሽኑ በዚህ ወር መጨረሻ በሚያካሂደው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ አጀንዳ አድርጎ በማቅረብ ውሳኔ እንዲያገኝ ጥረት መደረግ አለበት። ዛሬ ነገ ሳይባልም በአፋጣኝ ወደተግባር ተገብቶ ወራት ብቻ ለሚቀሩት የፓሪስ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን ብቻ የሚወክሉ ውጤታማ አትሌቶች እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል።

# ኮንታና ዳውሮ ፡ ድንቅ የተፈጥሮ እጅ ሥራ!

ከመንግስት ኮምኒኬሽን አገልግሎት
ኤልያስ ጌትነት እና እዮብ ሰለሞን

መስከረም 16 ቀን 2016 ዓ.ም ማለዳ ከአዲስ አበባ የተነሳው የጋዜጠኞች ቡድን ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የሚያደርገውን ጉዞ ጀምሯል። በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና በቱሪዝም ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተዘጋጀው የሚዲያዎች ጉዞ፤ የቱሪስት መዳረሻዎችን ማስተዋወቅ ዓላማው አድርጎ ወሊሶን ተሻግሮ፣ ወልቂጤን አቋርጦ፣ ጅማ አረፍ ብሎ በአመያ አዳሩን አድርጓል።

የጋዜጠኞቹ ቡድን በማግስቱ ጥቅምት 17 ደግሞ የግማሽ ቀን ጉዞ አድርጎ የኮይሻ የኃይል ማመንጫ ግድብ ግንባታን በመጎብኘት በኮንታ ዞን የሚያደርገውን ቅኝት ጀምሯል። በቀጣይ ቀናት ደግሞ ጨበራ ጩርጩራ ፓርክን፣ የኮይሻ ገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች የግንባታ ሂደትን፣ የዳውሮ ዞን ሙዚየምን፣ የድንጋይ ከሰል ማምረቻ ፋብሪካ፣ የሃላላ ኬላ ግንብና መዝናኛ ሎጅን ለተከታታይ አምስት ቀናት ተጎብኝተዋል። በዚህ የጉዞ ማስታወሻ የኮንታና ዳውሮ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ የቱሪስት መስህቦችን ከብዙ በጥቂቱ እንቃኛለን።

### የተፈጥሮ ግርማ ሞገስ

ተፈጥሮ ጥበቧንና ግርማ ሞገሷን የምትገልጥባቸው ጥቂት ሥፍራዎች አሉ። ጫካው ሳይመነጠር፣ ወንዞች ሳይበከሉ፣ ተራሮች ሳይናዱ፣ የዱር እንስሳት ሳይጠፉ፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች በሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ሳይዳቀሉ፣ ንፁህ የተፈጥሮ ውበትና ማራኪ ገፅታ ለማግኘት በተለይም በዚህ ዘመን አዳጋች ነው።

ዓለም በተፈጥሮ ሀብቶች ውድመት ምክንያት በተፈጠረ የአየር ንብረት መዛባት እየተጨነቀ ባለበት በዚህ ወቅት፤ ኮንታና ዳውሮ ዞኖች ድንግል የተፈጥሮ ሀብቶቻቸውን ይዘው "ኑ ተደመሙብኝ" ይላሉ። በእርግጥም በተፈጥሮ ውበት መማረክ የሚፈልግ ሰው ኮንታና ዳውሮ ዞኖችን ሊጎበኝ ይገባል።

በእነዚህ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ሲደርሱ በአራቱም አቅጣጫ በተራሮች ይከበባሉ። ከፊትዎ፣ ከኋላዎ እና ከጎንዎ አስደናቂ የተራሮች ሰንሰለት ይከብዎታል። ኮንታና ዳውሮ ፈጣሪ በተራራ ክምሮች የጻፋቸው ምድሮች ናቸው። በእነዚህ ማራኪ የተራራ ክምሮች መካከል መገኘት መንፈስን ያድሳል። ተራሮቹ የተላበሱት ጥብቅ ደን በወፎች ዝማሬ ጆሮዎትን ይማርካል፣ አረንጓዴነቱም የዐይን ምግብ ነው።

### የጨበራ ጩርጩራ ፓርክ

በኮንታና ዳውሮ ዞኖች ከሚገኙት አስደማሚ ቦታዎች የጨበራ ጩርጩራ ፓርክ አንዱ ነው። ኮንታና ዳውሮን የሚያጎራብተው ጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ በውስጡ አያሌ ወንዞች፣ ሀይቆችና ፏፏቴዎችን አቅፎ ይዟል። ይህም የሞቃታማውን አካባቢ ግለት እረስተው የመቀዝቀዝ ፋታ ለማግኘት ያስችላል። ጨበራ ጩርጩራ ፓርክ ከ137 በላይ የአዕዋፋት ዝርያዎችን፣ በቁጥር 57 መካከለኛና ትልልቅ አጥቢ የዱር እንስሳት አይነቶችን፣ ሀገር በቀል ጥንታዊ ዕፅዋትን፣ የተፈጥሮ ፍልውኃዎችን፣ ሐይቆችን፣ ፏፏቴዎችንና ሌሎች የተፈጥሮ መስህቦችን በውስጡ ይዟል። በፓርኩ የሚገኙ ፍልውኃዎች ለተለያዩ ህመሞች ፍቱን መድኃኒት ናቸው።

ጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ በደቡብ ምዕራብ ክልል በኮንታ እና በዳውሮ ዞኖች ውስጥ ይገኛል። ወደ ፓርኩ ለመጓዝ ከአዲስ አበባ በወላይታ ሶዶ ታርጫ ኢሰራ አልያም በአዲስ አበባ ጅማ አመያ መጓዝ ይቻላል።

ከአዲስ አበባ በጅማ 465 ኪሎ ሜትር ተጉዘው የሚያገኟት አመያ ከተማ የብሔራዊ ፓርኩ ደጅን ከሚባሉት ከተሞች አንዷ ናት። አመያ የኮንታ ዞን መዲና ስትሆን በደን የተሸፈነች፣ አስደናቂ የመልከዓ ምድር አቀማመጥ ያላት ለቅንጡ ሎጆች ምቹ በሆነ መልከዓ ምድር ላይ ያረፈች ከተማ ናት።

> ጨበራ ጩርጩራ ፓርክ ከ137 በላይ የአዕዋፋት ዝርያዎችን፣ በቁጥር 57 መካከለኛና ትልልቅ አጥቢ የዱር እንስሳት አይነቶችን፣ ሀገር በቀል ጥንታዊ ዕፅዋትን፣ የተፈጥሮ ፍልውኃዎችን፣ ሐይቆችን፣ ፏፏቴዎችንና ሌሎች የተፈጥሮ መስህቦችን በውስጡ ይዟል። በፓርኩ የሚገኙ ፍልውኃዎች ለተለያዩ ህመሞች ፍቱን መድኃኒት ናቸው

### አስደማሚው የሃላላ ኬላ ሪዞርትና የኮንታና ዳውሮ ታሪካዊ መስህቦች

የአካባቢውን የቱሪስት የስበት ማዕከላዊነቱን ወደ ዘመናዊ የቱሪስት መዳረሻ የቀየረው አዲሱ የሃላላ ኬላ ሪዞርት የተገነባው በዚህ በጨበራ ጩርጩራ ፓርክ አቅራቢያ ነው። የኦሞ ወንዝን ተንተርሶ የተገነባው ሃላላ ኬላ ሪዞርትም ዓለም አቀፍ ቱሪስቶችን ወደ አካባቢው የሚስብ ሌላኛው የገበታ ለሀገር ትሩፋት ነው።

ይህ ሪዞርት ምቹ ማረፊያዎች፣ መዋኛ ገንዳዎች፣ ሬስቶራንት፣ ባሕላዊና ዘመናዊ የግንባታ ጥበብ፣ የጀልባ ላይ ሽርሽር፣ ማራኪ ገፅታን የሚያመላክቱ ቴራሶች፣ በንጉሥ ሃላላ አማካይነት ከድንጋይ የተሠሩ ግንቦችን ጥበብ የሚያንፀባርቅ ግንባታ ወዘተ ያለበት ምቹ የቱሪዝም ሥፍራ ነው። ሪዞርቱ ዓለም አቀፍ የኮንፈረንስ ቱሪዝምን ለማስተናገድም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ታግዞ የተገነባ መኾኑ የመስህብነቱ ተጨማሪ ኃይል ነው።

በመስከረም ወር የሚከበሩት "ሀንግጫ" እና "ቶኪ በአ" የተሰኙት የኮንታና የዳውሮ ብሔረሰቦች የዘመን መለወጫ በዓላት ተጨማሪ የአካባቢው የቱሪዝም ሀብቶች ሲኾኑ፤ በዓላቱን በአካል ተገኝቶ ማክበርም ልዩ ትዕይንትና ትዝታ የሚሸመትበት ነው። በእነዚህ በዓላት የአካባቢዎቹ ጥንታዊና ባሕላዊ እሴቶች ከምንግዜውም በላይ የሚደምቁበት ነው።

### ሃላላ ኬላ፡ የኢትዮጵያ ታላቁ ግንብ

ከሃላላ ኬላ ሪዞርት ግንባታ ጋር የተካተተው የንጉሥ ሃላላ ግንብ በአካባቢው ያለ ሌላኛው ታሪካዊ ቅርስ ነው። የንጉሥ ሃላላ ድንጋይ ካብ (ሃላላ ኬላ) የተገነባበት ዋና ዓላማ ዳውሮን ከአጎራባች የፈረሰኛና እግረኛ ጦር ጥቃት ለመከላከል እንደሆነ ይነገራል። የድንጋይ ካቡ የጠላት መግቢያና መውጫ እንደሚሆኑ በሚገመቱ አካባቢዎች የጦር በሮች በማዘጋጀት፣ በእያንዳንዱ የጦር በር ጠባቂ ሹም (Miis'aa Iraasha) ሹመት በመስጠት፣ የግዛት ወሰንና የሕዝብ ደህንነት ለማስጠበቅ ነበር።

የካዎ ሃላላ ድንጋይ ካብ (ኬላ) መገኛ በዳውሮ ዞን ኦሞ ወንዝን ተከትሎ ነው። ከዳውሮ ዞን ወረዳዎች መካከል ኢሠራ፣ ዲሳ፣ ሎማ፣ ዛባ ጋዞ፣ ጌና፣ ታርጫ ከተማ አስተዳደርና ታርጫ ዙሪያ ወረዳዎችን በማካለል ጋሞ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ከምባታ ጠንባሮ፣ ጅማ ዞኖንና ኮንታ ዞን መሻገሪያ ድንበሮችን ያካለለ ታሪካዊ የዳውሮ ንጉሥ ጥንታዊ የኪነ-ሕንፃ ግንባታ ጥበብና የዳውሮ ሕዝብ የጥንካሬ መገለጫ ነው። የሃላላ ኬላ ግንብ ከ1532 እስከ 1822 ዓ.ም. በሀገር በቀል ዕውቀት የተገነባ ነው።

"ሃላላ" የዳውሮ ንጉሥ መጠሪያ ሲሆን፤ "ኬላ" የሚለው የድንጋይ ካብ (የመከላከያ ካብ) የሚል ትርጓሜ አለው። ካዎ ሃላላ ድንጋይ ካብ (ሀላላ ኬላ) በአንድ ረድፍ 175 ኪ.ሜ. እና አጠቃላይ ርዝመት በሰባት ረድፍ 1225 ኪ.ሜ. ይሸፍናል። ከ2.5 እስከ 5 ሜትር ስፋትና ከ2.5 እስከ 3.8 ሜትር በላይ ከፍታ አለው። በውበቱ አግራሞትን የሚፈጥረው ይህ ኪነ-ሕንጻ የዳውሮ ሕዝብን ጥንታዊ ሥልጣኔ የሚያሳይ ነው።

የግንባታው ሂደት 350 ዓመታት የፈጀው ሃላላ ኬላ ግንብ፤ ከ15ኛው እስከ 18ኛው ክ/ዘመን ዳውሮ ዞንን ያስተዳድሩ የነበሩ 14 ነገሥታት በቅብብሎሽ የገነቡት ነው። ከቻይናው 'ታላቁ ግምብ' እና ከፐርሺያው 'ባቢሎን' ጋር ተመሳሳይነት ያለው የድንጋይ ካብ አፍሪካ ውስጥ መኖሩ አስገራሚ ብቻ ሳይሆን ሰፋ ላለ ጥናት ይጋብዛል።

ሃላላ ኬላ የሚገኝበት የዳውሮ ዞን ከአዲስ አበባ በሻሸመኔ ወላይታ ሶዶ 455 ኪ.ሜ.፤ ከአዲስ አበባ በጅማ ደግሞ 479 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል።

### የኮንታና ዳውሮ ባሕላዊ መስህቦች

የኮንታና ዳውሮ አካባቢዎችን የቱሪዝም መስህብነት ከሚያጎሉ ጉዳዮች ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት የእንግዳ ተቀባይነት ባህል ነው። በአካባቢዎቹ የሚገኘው ማኅበረሰብ እንግዶችን በደስታና በእንክብካቤ ይቀበላል። ልክ እንደ ተፈጥሯዊ ንፁህ ውበቶቹ ኹሉ፤ የኮንታና ዳውሮ አካባቢ ማኅበረሰብም ከልብ በመነጨ አክብሮት እንግዶችን ተቀብሎ ያስተናግዳል። ይህም ጎብኚዎች ያለምንም ስጋት በአካባቢዎቹ ተገኝተው ለቀናት አሊያም ለሳምንታት በአካባቢው እንዲቆዩ ያደርጋል።

ኮንታና ዳውሮ ደርሰው የአካባቢውን ውብ ዜማና ውዝዋዜ መታደም ተጨማሪ ገፀ በረከት ነው። በባሕላዊ መሣሪያዎች የሚቀነባበረውን ሙዚቃ ከኦርጂናል ውዝዋዜ ጋር መመልከት ተጨማሪ የደስታ ምንጭ ይፈጥራል።

**"ቴመናይ ቴማ**
**ኤ ኮንታ ሴሜ"**
**"ዳውሮ ባና ዳውሮ ባና**
**ኤሰ ባና ኑኒ ባና"**

የሚሉትን ስንኞች በውብ ዜማ የማጣጣም ዕድል የሚገኘው በኮንታና ዳውሮ ምድር ሲገኙ ነው። ከእንሰት፣ ከቅቤና ከአይብ የሚሠሩ የአካባቢዎቹ ባሕላዊ ምግቦችም ሰውነትን የሚገነቡ፣ መልክን የሚያስውቡ ስለመኾናቸው የአካባቢው ነዋሪዎች በኩራት የሚመሰክሩት ሀቅ ነው። በዳውሮ ዞን የተገኘ የሥጋ አፍቃሪ የኾነ ሰውም ብርንዶ ሥጋ ከመኻል ከተማ በግማሽ በሚቀንስ ዋጋ መመገብ ይችላል።

የድንጋይ ከሰልም ሌላው የዳውሮ ዞን ተፈጥሯዊ ሀብት ነው። በድንጋይ ከሰል ልማት ለመሰማራት ለሚፈልግ ባለሀብት ዳውሮ ተመራጭ ቦታ ነው።

በኮንታና ዳውሮ ዞኖች ያለው እምቅ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ መስህብ ከአካባቢው አልፎ ለሀገር ልማትም ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። በተለይም በቱሪዝም ዘርፍ አካባቢው ያለው አቅም የመጪው ጊዜ የቱሪዝም ልማት መዳረሻ የሚኾን ነው። መንግሥት ትኩረት ከሰጣቸው አምሥት የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል አንዱ ቱሪዝም መኾኑ ደግሞ፤ በአካባቢዎቹ ላይ መዋዕለ ንዋይ እያፈሰሱ ላሉ እና ወደፊትም በዘርፉ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ኹሉ አበረታች ዜና ነው።

ውብ የተፈጥሮ ፀጋ የተጎናፀፈው ጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ፤ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት እየተገነቡ ካሉ የመዝናኛ ሎጆች ጋር ተዳምረው የአካባቢውን መስህብነት የበለጠ የሚያጎሉ ናቸው። ወደ ፓርኩ የሚያደርሱ የመንገድ መሠረተ ልማቶች እና የኮይሻ ገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች በተሟላ ሁኔታ ሲጠናቀቁ ለጎብኚዎች እጅግ ምቹ መዳረሻ ይኾናል።

እንደ ኮንታና ዳውሮ ኹሉ እምቅ የቱሪዝም ሀብት ያላቸውን አካባቢዎች በስፋት ማስተዋወቅ፣ የመሠረተ ልማት አውታሮችን በብዛት መዘርጋትና መዋዕለ ንዋይን ማፍሰስ ለዘላቂ ሀገራዊ ልማት እንዲሁም ለሀገር ገፅታ ግንባታ መሠረት ነው።

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ያሉ የቱሪስት መስህብና መዳረሻዎች በስፋት ቢታወቁና ሊጎበኙ እንደሚገባ ሥፍራዎቹን የጎበኙ ኹሉ ይመክራሉ። በአካባቢዎቹ የተገኙ ጋዜጠኞችም ይህንኑ ሀሳብ ይጋራሉ።

ኢትዮጵያ ተነብባ የማታልቅ መጽሐፍ፣ ተጽፋ የማትጨረስ ድርሳን ስለመኾኗ የደቡብ ምዕራብ አካባቢ ስነምህዳር የቱሪዝም ሀብቶች ምስክር ናቸው። በእነዚህ ሥፍራዎች ተገኝቶ ጉብኝት ማድረግ ከመዝናናትም በላይ ነው። ከንፁህ ተፈጥሮ ጋር መገናኘት፤ እንቁ ባህል ውስጥ መገኘት፣ የሀገርን አንድ ገፅ ማወቅ ለሚፈልግ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እጃቸውን ዘርግተው ይጠብቃሉ።

# የእደጥበብ ባለሞያዋ

ስምስም መንግሥቱ

ከቢለዋ ከፍ ባለ የሥለት መሣሪያ በመጠቀም፤ ቀርከሃውን እየሰነጠቁ ያዘጋጃሉ። ሥራቸውን በፍጥነት ሲያከናውኑ፤ የሚጠቀሙበት ሥለታም መሣሪያ ለአደጋ እንዳጋያልጣቸው የሚል ስጋት ውስጥ ይጨምራል። እጃቸው ሥራውን በመልመዱ ሳት እንኳን ሳይሉ፤ በፍጥነት በያዙት የሥለት መሣሪያ የመሰንጠቁን ሥራ ያከናውናሉ።

የተሰነጠቀው ቀርከሃም ቢሆን እጅ መውጋቱ አይቀርም። ቀርከሃውን ለማለስለስ ጥቅም ላይ የሚውለው ኬሚካልም ለመተንፈሻ አካል ጠንቅ መሆኑ አይቀሬ ነው። እነዚህን ሁሉ ነገሮች እያየ ያሰበ ሰው መጨነቁ አይቀርም። እርሳቸው ግን ከሥራው ጋር ከመለማመዳቸው የተነሣ አይጠነቀቁም። አልፎ አልፎ የሚጠቀሙበት ሥለታም መሣሪያም ሆነ የተሰነጠቀው ቀርከሃ እጃቸው ላይ ጉዳት ቢያደርስባቸው እንኳን በአልኮል ጠርገው ሥራቸውን ይቀጥላሉ፤ ጉዳቱን ምክንያት አድርገው ሥራቸውን አያቋርጡም።

በሥለታሙ መሣሪያ እየሰነጠቁ ባዘጋጁት ቀርከሃ በእንሥራ ቅርጽ ለጌጥና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ እንዲሁም የመብራት አምፖል መያዣ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ማስቀመጫ፣ ማቅረቢያዎችና የተለያዩ ቁሶችን ይሠራሉ። የሥራ ውጤቶቻቸውም ለእይታ የሚስቡና ውበት ያላቸው ናቸው። ጥንካሬያቸውም ቢሆን ከእንጨት ውጤቶች ያልተናነሰ እንደሆነ ገልጸውልናል። እንዲህ ያለውን የእጅ ጥበብ ሙያ የተካኑት ከታዳጊነት እድሜያቸው ጀምሮ በመሆኑ በሙያው ውስጥ ለረዥም ዓመታት ቆይተዋል።

በቀርከሃ የተለያዩ ነገሮችን መሥራትን በሥልጠና ያዳበሩት ሙያ ሲሆን፤ ሥራ የመቀጠር ዕድልም አስገኝቶላቸዋል። በኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው መሥራት የጀመሩት የቀርከሃ ባለሙያ በተፈለገበት ዘመን ነበር። ክህሎቱ፣ ልምዱና የሙያ ፍላጎቱ በሥራው ላይ ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ አድርጓቸዋል።

የእጅ ጥበበኛዋ ወይዘሮ ሙሉ ወንድሙ ይባላሉ። ሥለ የእጅ ጥበብ ሥራቸው፣ ልጅነታቸውንና እድገታቸውን፣ የቤተሰባቸውን ሁኔታ፣ ስለወደፊት እቅዳቸው አንስተን በሰፊው ተጨዋውተናል። የሙያ ባለቤት ብቻ ሳይሆኑ፤ የኑሮ ፈተናንም ተጋፍጠው ለመወጣት ያደረጉት ውጣ ውረድና ሥራ ወዳድነታቸው፣ ለሚሰሩበት ድርጅትም ያላቸው ተቆርቋሪነት ለሌሎችም አርአያ ሆነው አግኝተናቸዋል።

## ተወልደው ያደጉበት አካባቢና የኑሮ ሁኔታ

ወይዘሮ ሙሉ ወንድሙ እንዳጫወቱን፤ የተወለዱት በአዲስ አበባ ከተማ መርካቶ አካባቢ ነው። እድገታቸው ደግሞ ፈረንሳይ ለጋሲዮን በተለምዶ 41 እየሱስ ወይም አስራተ ካሳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰም ትምህርት ቤት ገብተዋል። ይሁን እንጂ ከ8ኛ ክፍል በላይ አልዘለቁም። የቤተሰባቸው የኑሮ ሁኔታ በጣም ያስጨንቃቸው ነበር። አባታቸው የቀን ሥራ ይሠሩ ነበር።

ገቢያቸው ቋሚ ባለመሆኑ ባዶ እጃቸውን ወደ ቤት የሚገቡበት ጊዜ ቀላል አልነበረም። እናታቸው የቤት እመቤት ናቸው። እናታቸው በስንደዶና አለላ ሰፌድ፣ መሶብና የተለያዩ የሥፌት ሥራዎችን እየሰሩ በመሸጥ በተጨማሪም በመኖሪያቸው አካባቢ ከሚገኝ ጫካ ውስጥ ቅጠል ጠርገው ለገበያ በማቅረብ ኑሮን ለመደጎም ጥረት ቢያደርጉም የሚገኘው ገቢ የቤተሰብ ኑሮን የሚያሻሽል አልሆነም። የቤተሰቡ የኑሮ ሁኔታ ከእለት ወደ እለት እየከበደ የእለት ጉርስም ለማሟላት ፈተና ሆነ። በዚህ የተነሳ የእርሳቸውና እህታቸውም የተለያዩ ፍላጎቶች ሊሟላላቸው አልቻለም። ወይዘሮ ሙሉ በየጊዜው የሚያዩትን ነገር መቋቋም አልቻሉም። ቤተሰባቸውን ለመርዳት፣ ለእርሳቸውና ለእህታቸው የሚያስፈልጋቸውንም ለማሟላት ትምህርታቸውን አቋርጠው ገቢ ሊያስገኝላቸው በሚችል ሥራ ላይ ለመሰማራት ወሰኑ።

የቤተሰባቸው የችግር ሁኔታ አስገድዷቸው ትምህርታቸውን እስከመተው ደረጃ የደረሱት ወይዘሮ ሙሉ፤ የሥራ ምርጫም አልነበራቸውም። እቅዳቸው እናታቸው ይሰሩ የነበረውን ከጫካ ውስጥ ቅጠል በመሰብሰብ ሸጠው ገቢ ለማግኘት ነበር። በመኖሪያ አካባቢያቸው በሚገኘው ደን ውስጥ ገብተው የረገፈ ቅጠል ጠርገው በማዳበሪያ ሞልተው አንዱን ሸክም በሁለት ብር ከሃምሣ ሣንቲም በመሸጥ ገቢ ማግኘት ጀመሩ። በወቅቱ ገንዘቡ ብዙ ነገር የመግዛት አቅም ስለነበረው የእለት ኑሮአቸውን መሸፈን ቻሉ።

ቅጠል ተሸጦ በቀን የሚገኘው ሁለት ብር ከሃምሣ ሣንቲም ከእለት ጉርስ ባለፈ የተሻለ ኑሮ ለመኖር የሚያስችል አይደለም። ነገር ግን አባታቸው በቀን ሸክም ደክመው፣ እናታቸው ደግሞ ስፌቱንም ቅጠል መልቀሙንም ጎን ለጎን በማስኬድ ቢሰሩም ኑሮ አልሞላ ብሏቸው ሲቸገሩ ማየታቸው ልባቸውን ይነካው ስለነበር ቤተሰባቸውን ማገዝ መቻላቸው ትልቅ ደስታ ፈጠረላቸው።

ለእርሳቸውና ለእህታቸው ጫማ እና አንዳንድ የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች በማሟላት ቤተሰብ አለማስቸገራቸውም ሌላው እፎይታ ነበር። ጫማም ሆነ ልብስ ከእህታቸው ጋር ተጋርተው በመጠቀም ለጊዜውም ቢሆን የነበረባቸው ችግር ተቃለለላቸው። ወይዘሮ ሙሉ እንዲህ ኑሮን ለመደጎም ለአራት ዓመታት ያህል ቅጠል ለቅመው ሸጡ።

## የእደጥበብ ሙያ ባለቤት የሆኑበት አጋጣሚ

ቅጠል ለቅመው መሸጡ የቀረላቸው፤ የተባበሩት መንግሥታት፣ የትምህርት፣ የሳይንስና ባሕል ድርጅት (ዩኒሴፍ) ውስጥ የእደጥበብ የሥልጠና ዕድል ካገኙ በኋላ ነበር። ድርጅቱ ትምህርታቸውን ላቋረጡ ተማሪዎች ስልጠና በመስጠት የሙያ ባለቤት እንደሚያደርግ ከእናታቸው መረጃ አገኙ። በድርጅቱ የሥልጠና ዕድል ለማግኘት ግን ነገሩ ቀላል አልነበረም። በወቅቱ ድርጅቱ የሚጠይቀውን የእድሜ መሥፈርት አያሟሉም ነበር።

ድርጅቱ ፍላጎታቸውንና ችግራቸውንም ግምት ውስጥ በማስገባት በእድሜያቸው ላይ አንድ ዓመት ጨምረው ለመመዝገብ ቻሉ። ድርጅቱ ተባብሯቸው እንጂ የሚቀበለው፤ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑትን ነበር። ይህ እድል ለወይዘሮ ሙሉ ተስፋን የሰነቀ ነበር። ትልቁ የልባቸው መሻት የቤተሰብን ኑሮ መቀየር በመሆኑ፤ የአንድ ባለሙያ ባለቤት ሆነው፣ በሙያው ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ መሰማራት በጣም የሚፈልጉት ስለነበር፤ ባገኙት ዕድል በጣም ተደሰቱ።

ድርጅቱ ሥልጠናውን ያመቻቸላቸው ቦታ ወይም ማዕከል ያኔ ሕዝባዊ ኑሮ እድገት ይባል እንደነበርም ያስታውሳሉ። እርሳቸው እንዳሉት፤ በድርጅቱ ይሰጥ የነበረው ሥልጠና የእንጨት ሥራ (ውድ ዎርክ) ሲሆን፤ ምርት ማምረትንም በአንድ ላይ ያጣመረ ስለነበር እንደኧርዋኧርዌ ያሉ የልጆች መጫወቻዎች የመሳሰሉ ለመዋዕለ ሕፃናት የሚሆን የእንጨት ውጤቶችን ያመርቱ ነበር። እንጨት ከመላግ ጀምሮ እስከ መግጠም ድረስ ያለውን ሂደት በመሰልጠናቸው የተሟላ ሥራ ይሰሩ ነበር።

ምርቶቹንም ድርጅቱ ድጋፍ የሚያደርግላቸው አካባቢዎች ድረስ በመሄድ የመትከሉንና የመግጠሙን ሥራ ጭምር ያከናውኑ ነበር። በዚህ ሥራም በአማራ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች ሄደዋል። የመጀመሪያውን ተሞክሯቸውን ግን አይዘነጉትም፤ ከቤተሰብ ተለይተው ከአዲስ አበባ ከተማ ወጥተው ሲሄዱ ፍርሃት አድሮባቸው ነበር። በወቅቱ በድርጅቱ ውስጥ የነበሩት ዝናሽ የሚባሉት አሰልጣኛቸው ኃላፊነት በመውሰዳቸው ቤተሰቦቻቸውም ፈቃደኛ ሆኑ። ድርጅቱ የእንጨት ውጤቶቹን ለእርዳታ የሚያውላቸው ቢሆንም፤ ክፍያ ያገኙ ስለነበር በሚያገኙት ገቢ ቤተሰባቸውን ይረዱ ነበር። ዓላማቸውንም ማሳካት ቻሉ። ይሁን እንጂ የሚያገኙት ገንዘብ ያሰቡት ያህል ኑሮ የሚቀይር ሆኖ አላገኙትም። በዚህ ሁኔታ ለአምስት ዓመታት በእንጨት ሥራ ላይ ቆዩ።

የእንጨት ሥራውን በዚህ ሁኔታ እያከናወኑ፤ ድርጅቱ የልዩ ስልጠና ፍላጎት አመቻቸ። የሥልጠናው አይነት ቀርከሃ፣ብረታ ብረት፣ አስሮ መንከር (ስዕል ስክሪን) ያካተተ ነበር። ወይዘሮ ሙሉ ከነዚህ የስልጠና አይነቶች ምርጫቸው ቀርከሃ ነበር። ነገር ግን የመረጡት ስለሙያው በቂ ግንዛቤ ኖሮአቸው አልነበረም። ባሳዩት ፍላጎት መሠረት ድርጅቱ እርሳቸውን ጨምሮ አምስት ሴቶች በምርጫቸው በቀርከሃ የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ሰለጠኑ። ሙያውን ለመቅሰምም ጊዜ አልወሰደባቸውም።

ፍላጎቱና ልጅነቱም ስለነበር፤ እንዲሁም በሙያው ተክነው የገቢ ማስገኛ በማድረግ ችግርንም ለመወጣት ጭምር አስበው ነበርና ስልጠናውን በትጋት ተከታተሉ። በሥልጠናውም ከአምስቱ ሰልጣኞች መካከል የተሻሉ ሆነው በመገኘታቸው አንደኛ ሆነው አጠናቀቁ። ድርጅቱ ውስጥ በቀርከሃ ግብአት የተለያዩ ነገሮች ቢሰሩም ሰልጣኞች እንዲሰለጥኑ የሚደረገው የተወሰነውን ብቻ ነበር። እርሳቸው ግን በሥልጠና ያላገኙትንም በመሞከር ለመሥራት ጥረት ያደርጉ ነበር።

ወይዘሮ ሙሉ አምስት ዓመት ከቆዩበት የእንጨት ሥራ በቀርከሃ ሰልጥነው ያገኙት ሙያ የተሻለ ሆኖ እንዳገኙት ይናገራሉ። እርሳቸው እንዳሉት የእንጨት ሥራ ማሽን ይፈልጋል። ቀርከሃ ደግሞ በአንድ ቀላል የእጅ መሣሪያ ወይንም በቢላዋ በመጠቀም የተለያዩ የቀርከሃ ውጤቶችን መሥራት ይቻላል። በልጅነታቸው እናታቸው በስንደዶና አክርማ የስፌት ሥራዎችን ሲሰሩ ስንደዶና አክርማውን በመሰንጠቅ ያግዟቸው ስለበር ይሄ ልምዳቸው የቀርከሃውን ሥራ ቀላል አድርጎላቸዋል።

ወይዘሮ ሙሉ፤ የአንድ ሙያ ባለቤት የሆኑት በዚህ ሁሉ ሂደት ነበር። ስልጠና ሰጥቶ የሙያ ባለቤት ባደረጋቸው ድርጅት ውስጥ እየሰሩ ያቋረጡትን ትምህርት ለመቀጠል በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ መከታተልም ጀምረው ነበር። ትምህርቱ ግን አልሆነላቸውም። በተለያየ ምክንያት አቋረጡ።

## በኢትዮጵያ ንግድ ሥራ ድርጅት ውስጥ የመቀጠር ሂደት

የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት በቀርከሃ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን እንደሚፈልግ ማስታወቂያ ማውጣቱን በተመለከተ መረጃው ደርሷቸው የተመዘገቡት አንድ በሚያውቃቸው ሰው አማካኝነት ነበር። በቀርከሃ ሙያ አብረዋቸው የሰለጠኑት ሴቶችም ለመወዳደር አብረዋቸው ተመዝግበው ነበር። በወቅቱም ያወዳደራቸው ሕዝባዊ ኑሮ እድገት የሚባል ተቋም ሲሆን፤ የሚፈለገው ሙያተኛ ሁለት ብቻ ነበር። በወቅቱ ስለነበረው ፈተናም እንዳስታወሱት፤ ፈተናውን የሰጣቸው የጃፓን ዜግነት ያለው ሰው ሲሆን፤ ፈታኙ በፊታቸው ሰርቶ ያሳያቸውን ዲዛይን መልሶ ደግሞ መሥራት ነበር። በተጨማሪ ደግሞ በአንድ ኢትዮጵያዊ የቃል ፈተና ቀረበላቸው። በውድድሩ ላይ ከቀረቡት መካከል አንዷ ሆነው አለፉ። ሌላኛዋ ደግሞ ወይዘሮ ሁሉሀገርሽ ዓለማየሁ ናቸው።

ሌሎች ተወዳዳሪዎች አብረዋቸው ለምዝገባ ቢቀርቡም፤ መስፈርቱን ባለማሟላታቸው ለፈተና ሳይቀርቡ ተሰናበቱ። እርሳቸውና የሙያ አጋራቸው ግን በእንጨት ሙያም መሰልጠናቸው መስፈርቱን ለማሟላት አግዟቸዋል። በዚህ ሁኔታ ወይዘሮ ሙሉና ሁሉሀገርሽ ፈተናውን አልፈው በኢትዮጵያ ንግድ ሥራ ድርጅት ተቀጥረው በእደጥበብ ሥራ ክፍል ውስጥ ተመደቡ። ከተቀጠሩበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በዚሁ ክፍል ውስጥ በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

ወይዘሮ ሙሉ አሁን የሚሰሩበት ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት እርሳቸው በተቀጠሩበት ዘመን፤ በሌ አካባቢ ይገኝ ነበር። በዚህ ተቋም ውስጥ መቀጠራቸው ብቻ ሳይሆን፤ አካባቢውም ለእርሳቸው የተሻለ ሆኖ አገኙት። እርሳቸው የሚኖሩበት ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ እንደዛሬው የለማ ባለመሆኑ፤ የማሕበረሰቡ አኗኗር ከገጠር የተለየ አልነበረም። ውሃ ከምንጭ እየቀዱ ይጠቀሙ ነበር። የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ቢኖርም በአንድ ቆጣሪ ብዛት ያለው ሰው ይጠቀም ነበር። የኤሌክትሪክ ኃይል ሲቋረጥ እንኳን ማሕበረሰቡ የሚጠቀመው ኩራዝ ነበር።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል



ፎቶ- ስምስም መንግሥቱ

ወይዘሮ ሙሉ ወንድሙ

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# የእደጥበብ....

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

ሻማ እንኳን አልነበረም። የትራንስፖርት አገልግሎትም ባለመኖሩ፤ በእግር መጓዝ የተለመደ ነው።

**የትዳር ሁኔታ**

መኖሪያቸው የቀበሌ ቤት ቢሆንም፤ አባታቸው በሕይወት እያሉ ግቢው ውስጥ ሰፊ ልማት ያካሂዱ ስለነበር አኗኗሩ ወደ ገጠርነት ያመዝናል። እርሳቸው ሥራ ከመቀጠራቸው ከሁለት ዓመት በፊት አባታቸው አርፈው፤ ‹‹ይህች ልጅ የሴት ልጅ እንዳትባል ባል ማግባት አለባት›› ተብለው በቤተሰብና በጎረቤት ግፊት ነበር ያለምርጫቸው ወደ ትዳር የገቡት። የትዳር አማጭያቸውም በእድሜ የሚበልጧቸው ግን ደግሞ እንደ ጓደኛ የሚቀርቧቸው በአቅራቢያቸው የሚኖሩ ሴት እንደነበሩና እኚህ ሴትም የባላቸውን ጓደኛ እንዲያገቡ ግፊት በማድረጋቸውና የእናታቸውንም ፈቃድ ለመሙላት ሲሉ ለትዳር እንደበቁ አጫወቱን።

የትዳር አጋራቸው ሥራቸው ጥበቃ በመሆኑ ደመወዛቸው ሁለቱንም በበቂ ሁኔታ ሊያኖር የሚችል ባለመሆኑ የቤት ኪራይ ወጪን ለመቀነስ በቤተሰባቸው ግቢ ውስጥ መኖር ግድ ነበር። ትዳር መሥርተው መልሰው ከቤተሰብ ጋር መኖሩ፤ በኑሮም ቢሆን የተሻለ ነገር ስላልገጠማቸው ጥሩ ስሜት አልፈጠረባቸውም። በተለይም ከቤተሰባቸው ጋር ሲኖሩ የኑሮ ሁኔታው ያስከፋቸው ነበር።

የሕይወት እጣ ፈንታን ከመቀበል ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም። በፈቃዳቸው ባይሆንም፤ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ የሆነውን የትዳር ኃላፊነትንም ተያያዙት። በተራራቀ ጊዜ ቢሆንም አራት ልጆች ተወለዱ። ዛሬ ልጆች አድገው ኃላፊነቱ ሲቀል ነገሮች እንደዋዛ ያለፉ ይምሰሉ እንጂ በአነስተኛ ገቢ ኑሮን ማሸነፍ ለወይዘሮ ሙሉ ከባድ ነበር።

ወይዘሮ ሙሉ እንዲህ ካለው የኑሮ ውጣ ውረድ እና የአኗኗር ዘይቤውም ቢሆን የገጠር አይነት ከመሰለው፤ አካባቢ ውስጥ በማሳለፋቸው ሥራ ሲቀጠሩ በወቅቱ የተቀጠሩበት መሥሪያ ቤትም ሆነ ድርጅቱ የሚገኝበት አካባቢ የተለየ ሆኖ አገኙት። በወቅቱ የፍርሃትም የደስታም የተዘበራረቀ ስሜት ነበራቸው። ፍርሃቱ ከገጠር ቀመስ አካባቢ መምጣታቸው ከሥራው አካባቢ ጋር እስማማለሁ አልስማማም? የሚል ነበር።

ደስታው ደግሞ በከተማ ውስጥ በትልቅ ድርጅት ውስጥ ሥራ ማግኘታቸው ነበር። ሌላው የባለቤታቸው የገቢ ምንጭ አነስተኛ በመሆኑ ሥራ መያዛቸው እፎይታን ስለፈጠረላቸው ተደሰቱ። በወር የሚያገኙት ደመወዝ 285 ብር መሆኑ ደግሞ ደስታቸው ወደር አልነበረውም። እርሳቸው እንዳሉት በዛ ጊዜ ከዩኒቨርሲቲ በዲፕሎማ የተመረቀ የሚያገኘው የደመወዝ መጠን ነበር። ደስታቸውን በታዳጊነት እድሜያቸው ሆነው ጫካ ውስጥ ቅጠል አብረዋቸው ሲለቅሙ ለነበሩ ብቻ ማካፈል በቂ ሆኖ አላገኙትም። ‹‹ለማን ልንገር?›› እስከማለት ደርሰው ቅጠል የሚለቅሙበት ጫካ ውስጥ በመሄድ ለጉቶ ሳይቀር እስከመናገር ደርሰዋል። የያኔው ደስታቸውን ዛሬም አልፎ እምባ እየተናነቃቸው በሲቃ ያስታውሱታል።

በወቅቱ በተመደቡበት የሥራ ክፍል ውስጥ ያገኟቸው አንድ ኢትዮጵያዊና የጃፓን ዜግነት ያለው ሰውን ነበር። ሥራውን በማለማመድም ሆነ በማበረታታት በጥሩ ሁኔታ ተቀበሏቸው። ጃፓናዊው ግን ብዙ አብሯቸው አልቆየም። በ1983 ዓ.ም የነበረው ወታደራዊ የመንግሥት ሥርዓት በሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ሲተካ፤ በነበረው የሥርዓት ለውጥ ምክንያት ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

ወይዘሮ ሙሉ፤ መሥሪያቤታቸውንም አካባቢውንም እየተለማመዱ ሲሄዱ ፍርሃቱ እየለቀቃቸው፤ በሥራቸውም ትጉህ እየሆኑ ረጅሙን የእድሜውን ጊዜያቸውን በኢትዮጵያ የቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት ውስጥ አደረጉ። በነበራቸው የሥራ ቆይታም ከቀርከሃ አልጋ፣ መደርደሪያ፣ ወንበር፣ ለተለያዩ ማስዋቢያዎችና አገልግሎቶች የሚውሉ ሥራዎችን በመሥራት ለድርጅቱ አንድ የገቢ ምንጭ እንዲሆን በማድረግ የሙያ ግዴታቸውን ተወጥተዋል። አሁንም በሥራቸው እየተጉ ይገኛሉ።

የቀርከሃ ሥራ ጥንቃቄና ፍላጎት እንደሚያስፍልገውም ነግረውናል። ቀርከሃ በባሕሪው ስኳርነት ስላለው በብል ይጠቃል። በብል እንዳይበላ ይጠቀሙበት የነበረው በእሳት መለብለብ፤ አሁን ላይ ግን በኬሚካል በመዘፍዘፍ ችግሩ እንዲወገድ ያደርጋሉ። በዚህ መልኩ ከተዘጋጀ በኋላ አልጋ፣ ወንበርና ለሌሎችም አገልግሎቶች የሚውሉ ሥራዎችን ይሰሩበታል። በተለያየ ቀለም መጠቀም



ሲያስፍልግም ቀለም አዘጋጅተው በመንከር ይጠቀማሉ።

ለመብሻ የሚውል ድሪል ከሚባለው መሣሪያ ውጭ ሥራው ባሕላዊ እንደሆነ ወይዘሮ ሙሉ ነግረውናል። ዋና የሥራ መሣሪያቸው ከቢለዋ ከፍ ያለው ለመሰንጠቂያ ሲጠቀሙበት የነበረው መሣሪያ ነበር። ሥራ ሲቀጠሩ በጀመሩበት መሣሪያ አሁንም እየተጠቀሙበት ነው። ሥለታም መሣሪያው ከጃፓን የመጣ ነው።

በዘመናዊ መሣሪያ አጠቃቀም ያልተተካውና በዚህ ባሕላዊ አሰራር የመቀጠሉን ሁኔታ እርሳቸው ምላሽ የሚሰጡበት ባይሆንም፤ ተቋማቸው በተለያየ አካባቢ እንዲዘዋወር መደረጉ አንዱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ።

ወይዘሮ ሙሉ ለተቋማቸው ልዩ ስሜት አላቸው። በሥራ ቆይታቸው ለእርሳቸው ትልቁ ቁምነገር ልጆቻቸውን ማሳደግ መቻላቸው ነው። እርሳቸው እንዳሉት የመጀመሪያ ልጃቸውን በሆቴል አስተዳደር አስተምረው በመጀመሪያ ዲግሪ አስመርቀዋል። ሁለተኛ ልጃቸው በትምህርቱ ባይገፋም የእርሳቸውን የእጅ ሙያ ቀስሞ እየሰራበት ይገኛል። ሁለቱ ሴቶች ልጆች ገና ተማሪ ናቸው። ልጆቻቸው ከእርሳቸው የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ በምክርም ጭምር የሚችሉትን በማድረግ ጥረት እያደረጉ ነው።

**ለሙያቸውና ለሚሰሩበት ተቋም ያላቸው ተቆርቋሪነት፤**

"የቀርከሃ ሙያ ሁሉ ነገሬ ነው" የሚሉት ወይዘሮ ሙሉ፤ ሙያውን ከኑሮቸው ጋር በእጅጉ አቆራኝተውታል። ተቀጥረው የሚሰሩበት ድርጀት የሚጠብቅባቸውን ኃላፊነት ይወጣሉ። ከሥራ በኋላ ወደቤታቸው ሲመለሱም የጓዳ ሥራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ መኝታ ሳይሆን፤ ወደ ሥራ ያመራሉ። ኑሮን ለመደጎም ተጨማሪ ገቢ ግድ በመሆኑ ከመኝታ ጊዜያቸው ቀንሰው ለሥራ ያውላሉ።

ለሙያው ያላቸው ፍላጎት እንቅልፍ ይነሳቸዋል። ለየት ያለ ዲዛይን ሲያዩ አያልፉም። በሌላ ግብአት የተሰራ እንኳን ቢሆን፤በቀርከሃ ግብአት ለመሥራት ጥረት ያደርጋሉ። አዲስ ዲዛይን ለመሥራት ድርጅታቸው ውስጥ ፍቃድ ባያገኙ እንኳን በግላቸው ሰርተው ለተጠቃሚ ያቀርባሉ። ስለሙያቸውም ሆነ ሥለትጋታቸው የሚያውቋቸው አንዳንድ ድርጅቶችም ለሙያ ተሞክሮ እየጋበዟቸው ሙያቸውን ያካፍላሉ። እግረ መንገዳቸውንም ከድርጅታቸው ውጭ እና እርሳቸውም በግላቸው ሰርተው ከሚያቀርቡት የተለየ ነገር ለመፈተሽ ዕድል የሚያገኙበት አጋጣሚን ያገኛሉ። ወደ ኋላ መለስ ብለው በትምህርት አለመግፋታቸው ይቆጫቸዋል። ተምረው ቢሆን አንዳንድ ቴክኖሎጂዎችንና የሌሎች ሀገሮችንም ተሞክሮ ለማወቅ ትምህርቱ ይጠቅማቸው እንደነበር የተገነዘቡት አሁን ነው። የትምህርት ጊዜ ቢያልፍባቸውም ክሕሎታቸውን ለመጠቀም ግን ወደኋላ አይሉም። አእምሮአቸውም አዳዲስ ነገር ለመቀበል ዝግጁ እንደሆነ ይናገራሉ።

የቀርከሃ ሥራ በሚፈለገው ልክ አድጓል ብለው አያምኑም። ብዙ መሰራት እንዳለበት ይሰማቸዋል። ሙያው ግለሰብንም ሀገርምን የሚጠቅም እንደሆነና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ትምህርት ሊሰጥ ይገባል ይላሉ። በተለይ ደግሞ ብዙ ነገር አግኝቼበታለሁ ብለው የሚመሰክሩለት የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት የበለጠ ሙያውን የሚያሳድግበት እድሉ ቢኖረውም ግን ስሙን ተጠቅሞበታል የሚል እምነት የላቸውም። ድርጅቱ በእርሳቸውም እንደተጠቀመ አድርገው አያስቡም።

ወይዘሮ ሙሉ ስለድርጅታቸው ተናግረው አይጠግቡም። በጥሩ ስም የተገነባ ነው ይላሉ። እርሳቸው ባይደርሱባቸውም ኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅትን የመሠረቱት አቶ ኃብተስላሴ ታፈሰ እንደሚባሉ፤ ኢትዮጵያ የ13 ወር ፀጋ ተብላ ስሟ እንዲጠራ ያደረጉ፣ የቱሪዝም አባትም እንደሚባሉ፣ የእደጥበብና የሥነጥበብ ውጤቶችም በውጭው ዓለም ሳይቀር እንዲታወቅ በማድረግ ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው ታሪኩን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ድርጅታቸው የቀድሞውን ገናና ስሙን ይዞ ጥሩ የሆነውን ታሪክ በተሻለ አስቀጥሎ ቢያዩ ምኞታቸው ነው።

አሁን ላይ ግን አንዳንድ ክፍተቶች ማየታቸው እያሳዘናቸው ነው። ድርጅቱ በተለይ በእደጥበብ ክፍል ውስጥ ይሰሩ የነበሩና ስም ካገኙባቸው አንዱ የሆነው አሻንጉሊቶች እንደነበሩ ያስታውሳሉ። እርሳቸው እንዳሉት በሚሰሩት አሻንጉሊቶች የባህል አልባሳት፣ ሙዚቃና ሌሎችም የኢትዮጵያን ባህል የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቶ ይቀርብ ነበር። አሁን ላይ አሻንጉሊቶች እየተሰሩ አይደለም። ባለሙያዎች በጡረታና በተለያየ ምክንያት ከተቋሙ ሲወጡ ሌሎች ባለሙያዎች አይተኩም። ምክንያቱን ባያውቁም የድርጅቱ የሥራ ቦታ በአንድ ላይ አለመሰባሰቡ አንዱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይጠረጥራሉ።

በአጠቃላይ ድርጅቱ እንደቀዳሚነቱ ትኩረት አልተሰጠውም ብለው ያምናሉ። በሌሎችም ዘርፎች ላይ የሚገኙ ባለሙያዎች እንዲሁ በቁጥር አነስተኛ እንደሆኑና እርሳቸው በሚሰሩበት ክፍልም እርሳቸውና አለቃቸው ወይዘሮ ሁሉሀገርሽ ብቻ መቅረታቸውን ነው የነገሩን። ባለሙያዎችን መተካት ካልተቻለ ድርጅቱ ስም ያፈራባቸውን ሥራዎቹን እንዳያጣ ይሰጋሉ።

በሥራ ዓለም ክፉም ደግም ያልፋል። ወይዘሮ ሙሉም በሁሉቱም ያሳለፏቸውን እንዲህ አስታውሰዋል። « ይሄን ያህል እንደከፉ በቅሬታ የማነሳው ነገር የለም። በሥራ ያደኩበት፣ ኑሮዬንም የመራሁበት ድርጅት በመሆኑ የሚበልጡብኝ መልካም የሆኑ ነገሮች ናቸው። ግን ደግሞ ቅሬታ አይጠፉም። ገና ሥራ እንደተቀጠርኩ ነበር ልጄ በእሳት ቃጠሎ ጉዳት ደርሶበት ለማስታመም፤ የቅርብ አለቃዬን ፍቃድ ጠየኩት። አልፈቅድም አለኝ። በጣም ከፋኝ። አለቀስኩ። ከአቅሜ በላይ ሆኖብኝ ወደ በላይ ሄድኩ። ከአለቃዬ የበላይ የነበሩ ሴት ኃላፊ ግን አይዞሽ ብለው ፈቅደውልኝ ልጄን ለማስታመም ቻልኩ። የእርሳቸው መልካምነት ተሰምቶኝ የነበረውን መጥፎ ስሜት እንድረሳው አደረገኝ።

የዛሬ ሰባት ዓመት ደግሞ ሌላ ከባድ ነገር ገጠመኝ። እናቴ በጠና ታማብኝ እርስዋን ለማስታመም አሁንም ፍቃድ ያስፈልገኝ ነበር። በዚህ ጊዜም ድርጅቴ የዋለልኝን ውለታ አልረሳውም። እናቴን ለሶስት ወራት ያህል ሳስታምማት ታግሶኛል። እንደአጋጣሚ እናቴ በሕይወት ልትተርፍልኝ አልቻለችም። በሞት ስትለየኝ። ድርጅቴ በሀዘኔም ጊዜ ከጎኔ ነበር። መላው የድርጅቱ ሰራተኛ የሀዘኔ ተካፋይ ነበር። ይሄ የማልረሳው ውለታ ነው። በማለት በመልካም አንስተዋል።

በአንድ ወቅትም በውስጥ በተካሄደ የሥራ ውድድር በትምህርት ምክንያት እድገት ሳያገኙ የቀረቡትን አጋጣሚም አንስተው፤ ሞራላቸው ተነክቶ እንደነበር ገለፁልን። እርሳቸው እንዳሉት፤ ድርጅቱ የአገልግሎት ዘመን ይያዝላችኋል የሚል ተስፋ አሳድሮባቸው ትኩረት አድርገው ሲሰሩ የነበረው በሙያቸው ላይ ብቻ ነበር። ለትምህርት ትኩረት እንዳይሰጡ በመዘናጋታቸው ባለሙያ በሚል መደብ መቆየታቸውን አጫወቱን። በወቅቱ ቅሬታ ቢፈጥርባቸውም ‹‹የሙያ ባለቤት ነኝ። በግሌም ሰርቼ እኖራለሁ›› በሚል እራሳቸውን እንዳጽናኑም ነግረውናል። አብረዋቸው ሥራ የተቀጠሩትና አሁንም አብረዋቸው እየሰሩ ያሉት ወይዘሮ ሁሉሀገርሽ ዓለማየሁ ግን ትምህርት ተምረው ስለበለጧቸው አሁን አለቃቸው ሆነዋል።

**የወደፊት እቅዳቸው**

በግላቸውም ቢሆን የቀርከሃ ሥራን አንድ ደረጃ በማድረስ የልባቸውን ለመሙላት ፍላጎት አላቸው። 55 ዓመት ሲሞላቸው የጡረታ መብታቸውን አስከብረው እድሜያቸው እስከፈቀደላቸው ድረስ በመሥራት ሙያውን ማስቀጠል፣ ለሀገራቸውም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት፣ በኑሮአቸውም ቢሆን ተሽሎ የመገኘት እቅድ አላቸው፤ አሁን 54ኛ ዓመት እድሜ ላይ ስለሆኑ በሚቀጥለው ዓመት እቅዳቸውን ለማሳካት አስበዋል። እድሜና ጤና ሰጥቷቸው የልባቸው መሻት እንዲሞላላቸው ተመኘተንላቸው ተሰነባበትን።

ዜና

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የንኢሌ ፓልም ስፕሪንግ ሉጅ ፕሮጀክትን አስጀመሩ

## - በአፋር ክልል የበጋ ስንዴ ምርት ሥራ ተጀምሯል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የገበታ ለትውልድ አካል የሆነውን የንኢሌ ፓልም ስፕሪንግ ሉጅ ፕሮጀክት በአፋር ክልል አስጀመሩ። በአፋር ክልል ዱብቲ ወረዳ የበጋ ስንዴ ምርት ሥራም በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካኝነት ተጀምሯል።

ፕሮጀክቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከጀመሯቸውና ካከናወኗቸው የገበታ መርሃ ግብሮች በሶስተኛው ዙር ሊገነቡ ከታቀዱ ሰባት የቱሪዝም መዳረሻዎች የንኢሌ ፓልም ስፕሪንግ ሉጅ የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት አንዱ መሆኑን ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከልዑክ ቡድናቸው ጋር በመሆን የልማት ሥራዎችን ለመገምገምና የበጋ ስንዴ ምርት ሥራን ለማስጀመር አፋር ክልልን ጎብኝተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአፋር ክልል፣ ዱብቲ ወረዳ በመገኘት የበጋ ስንዴ ምርት ሥራን ሲያስጀምሩ፤ በአካባቢው በመስኖ የሙዝ ተክል ልማት እየተከናወነ መሆኑን ተመልክተዋል።

በክልሉ አዲስ ልምድ በሆነው የፍራፍሬ እርሻ ሥራ የተሰማራ አርሶ እና ከፊል አርብቶ አደር ሥራዎች በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተጎብኝተዋል።

በዱብቲ ወረዳ ኅብረተሰቡ በስምንት ሺህ ሔክታር መሬት ላይ የበጋ ስንዴ ለማምረት ዝግጅት ማድረጉን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስታውቋል።

በተያዘው ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ በሶስት ሚሊዮን ሔክታር ላይ የበጋ ስንዴ ለማምረት ዕቅድ መያዙም ተመላክቷል።

በዋናነት በአርብቶ አደርነት የሚታወቀውና በግብርና ግብዓቶች የቀዳሚ ድጋፍ መዳረሻ ያልሆነው የአፋር ክልል፤ በአሁኑ ወቅት በሀገር አቀፉ የግብርና ምርታማነት ላይ በስንዴ፣ በጥጥና በሙዝ ምርት አስተዋፅዖው ከፍ እያለ መምጣቱ ተገልጿል።

በአፋር ክልል የልማት ሥራዎች ምልከታቸውን በመቀጠል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በክልሉ ዋርሰሶ ወረዳ የሚገኘውን የቤንቶኒቴ ማዕድን ማውጫና ማምረቻን ጎብኝተዋል።

ቤንቶኒቴ ለሴራሚክና ቀለም ብሎም ለመሰል ምርቶች ጠቀሜታ በመዋሉ "ትንግርታዊ ርጥብ አፈር" እና "ብዝሃ ጥቅም ያለው ሸክላ አፈር" በመባል በአድናቆት የሚነሳ ሀብት መሆኑ በጉብኝቱ ወቅት ተገልጿል።

# ናሽናል አቪዬሽን በዘርፉ ብቁ ባለሙያ የማፍራት ተግባሩን አጠናክሮ እንዲቀጥል ተጠየቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ በዘርፉ ብቁ ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ እንዲቀጥል ተጠየቀ። ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ በተለያየ ዘርፎች ያሠለጠናቸውን 943 ተማሪዎች ትናንትና አስመርቋል።

በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ የአካዳሚክ ጉዳዮች ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኤባ ሚጀና (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ በተለያዩ ሙያዎች ተማሪዎችን ተቀብሎ በማሠልጠንና ብቁ ምሩቃንን በማፍራት ረገድ እያከናወነ ያለውን ውጤታማ ሥራ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

ሀገሪቷ በዘርፉ ብቁና የሠለጠኑ ባሙያዎች በብዛት ያስፈልጓታል ያሉት ዶክተር ኤባ፤ በዚህ ረገድ ኮሌጁ እያከናወነ የሚገኘው ሥራ የተለያዩ አየር መንገዶችንም የሚደግፍ በመሆኑ ሊበረታታ ይገባዋል ብለዋል።



በፍጥነት እያደጉ የመጡትን የአቪዬሽንና የቱሪዝም ኢንዱስትሪዎች ቀጣይነት ለማረጋገጥና ተወዳዳሪነቱን ለማሳደግ ቁልፍ የሆነውን የሠለጠነ የሰው ሃይል በማፍራት ረገድ ኮሌጁ የሚያከናውናቸውን ሥራዎች እያሳደገ መሄድ እንዳለበት አመላክተዋል።

የናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ ፕሬዚዳንት ደርበው በለው (ፐ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ኮሌጁ ከሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ዕውቅና ባገኘባቸው በአቬዬሽን ዘርፍ ትምህርቶች እንዲሁም በተለያዩ የትምህርት መስኮች ያሠለጠናቸውን 943 ተማሪዎች አስመርቋል።

በተጨማሪ ተመራቂዎቹ በሆቴል ማኔጅመንት፣ አካውንቲንግና ፋይናንስ፣ በማርኬቲንግ እና በበረራ አስተናጋጅ እንዲሁም በእንግዳ አቀባበል የትምህርት ፕሮግራሞችን የሠለጠኑ መሆኑን አመላክተዋል።

ኮሌጁ ከዓለም አቀፉ የአየር ትራንስፖርት ማኅበር (IATA) እና እንግሊዝ ሀገር ከሚገኘው ኢንስቲትዩት ኦፍ ኮሜርሺያል ማኔጅመንት (ICM) ባገኘው ዕውቅና መሠረት ከአቪዬሽን እንዲሁም ከቱሪዝምና ሆቴል ሙያ ጋር በተገናኙ ትምህርት ደረጃቸውን ያሟሉ ዓለም አቀፍ ሥልጠናዎችን እየሰጠ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሰርተፍኬት፣ በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቁ ተማሪዎች ሀገራቸውን በቅንነት በማገልገል ይበልጥ ውጤታማ ለመሆን ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ እንዳለባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

# "የአዳዲስ ክልሎች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ በምሥረታ በዓሉ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ የአዳዲስ ክልሎች መመሥረት የሕዝቦችን ሕገ-መንግሥታዊ መብት በማክበር የመልማት ጥያቄያቸውን ምላሽ የተሰጠበት ነው።

አዳዲስ የክልል አደረጃጀት ሲሰጥ የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻልና በሀገሪቱ ጠንካራ ሥርዓት ለመገንባት እንደሆነ ሊሰመርበት እንደሚገባ አቶ አደም ጠቁመዋል።

አደረጃጀት በራሱ ግብ አይደለም ያሉት የፓርቲው ምክትል ፕሬዚዳንት፤ ከሀገር እና ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም አኳያ በጥንቃቄ መሥራት እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

እንደ አቶ አደም ገለጻ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግና ዕውን ለማድረግ ተስፋ የተጣለበት ነው።

ክልሎች እርስ በእርሳቸው በሚፈጠሩ መስተጋብር ችግሮችን የመፍታት እሴት ማዳበር አለባቸው ያሉት አቶ አደም፤ በሕዝብ ይሁንታ ያገኙ አመራሮችን ለማብቃት ፓርቲያቸው ቁርጠኛ መሆኑን ተናግረዋል።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው በበኩላቸው፤ የክልሉ መመሥረት ለዘመናት የሕዝቦች ጥያቄ ሆኖ የነበረው እራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ መልስ ያገኘበት ነው ብለዋል።

መንግሥት ሁሉንም በጋራ የማልማት መርህ አድርጎ እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረው፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከተመሠረተ በኋላ የክልሉ ሕዝብ ሙሉ አቅሙን በልማት ላይ ሊያተኩር እንደሚገባ አመላክተዋል።

በክልሉ ሰባት ብዝሃ ከተሞች ወደ ሥራ መግባታቸውን ገልጸው፤ በከተሞቹ ሙሉ መንግሥታዊ አገልግሎቶችን ለማስጀመር እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል። አቶ እንዳሻው አክለውም፤ በክልሉ በየዘርፉ የሚገኙ አመራሮች የሕዝቦችን የመልማት ጥያቄ ለመመለስ ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል።

ባለሀብቶችና መላው የክልሉ ሕዝብ በአጭር ጊዜ ለውጥ ለማምጣት በአንድነት እንዲረባረቡ ጥሪ አቅርበዋል። የተለያዩ ክልሎች አዲስ ለተቋቋመው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከ399 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርገዋል። የተለያዩ የክልል ፕሬዚዳንቶችና የከተማ መስተዳድሮች የኢትዮጵያን ብልፅግና ዕውን ለማድረግም በጋራ ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በመርሃ-ግብሩ የተለያዩ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል። የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ነሐሴ 13 ቀን 2015 ዓ.ም በሰባት ዞኖችና በሦስት ልዩ ወረዳዎች በክልልዊ መንግሥት እንዲደራጅ መወሰኑ የሚታወስ ነው።

# ‹‹የክልሉን ጸጥታ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የክልሉን ሰላም ለማስጠበቅና ወደነበረበት ለመመለስ መከላከያ ሠራዊት የክልሉን የጸጥታ አካላት በማስተባበር ሰፊ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል። የክልሉን ጸጥታ ለመስጠበቅ ከሚከናወኑ ተግባራት ጎን ለጎንም የልማት ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ እየተሠሩ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በነበሩ ግጭቶች የሰዎች እንቅስቃሴ ተገድቦባቸው በነበሩ አካባቢዎች ሰላም እንዲሰፍንና መደበኛ እንቅስቃሴ እንዲጀመር ማድረግ ተችሏል ያሉት ዶክተር መንገሻ፤ ይህም አርሶ አደሩና ሌላው የህብረተሰብ ክፍል ተንቀሳቅሶ የየዕለት ተግባሩን እንዲያከናውን ምቹ ሁኔታ ፈጥሮለታል ብለዋል።

የክልሉ መንግሥት የክልሉን ጸጥታ ለማስጠበቅ ከሚከናወኑ ተግባራት ጎን ለጎን የልማት ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ እንዲከናወኑ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በተለይ የግብርና ሥራዎች ወቅቱን ተከትሎ እንዲከናወኑ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ አሁን ላይ የደረሱ ሰብሎች እንዲሰበሰቡ ለማድረግ በየደረጃው ያለው አመራር አርሶ አደሩን ጋር በቅርበት እያገዘ መሆኑን አብራርተዋል።

ትምህርት ቤቶች ተከፍተው ተማሪዎችን ተቀብለው ማስተማር መጀመራቸውን ገልጸው፤ የጤና፣ የንግድና ሌሎችም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተከፍተው ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል ብለዋል።

አጋጣሚውን ተጠቅመው የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ ነጋዴዎችን ለመቆጣጠርና የዋጋ ንረትን ለመከላከል አስፈላጊው የክትትልና ቁጥጥር ሥራ እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል።

በግጭቱ ምክንያት ሥራ አቁመው የነበሩ የኢንቨስትመንት ተቋማት ሥራ እንዲጀምሩ ተደርጓል ያሉት ዶክተር መንገሻ፤ ጉዳት የደረሰባቸው የኢንቨስትመንት ሥራዎችም ተጠግነው ወደ ሥራ እንዲመለሱ የክልሉ መንግሥት አስፈላጊውን እገዛ እያደረገ መሆኑን አብራርተዋል።

በከተሞች የሚከናወኑ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችም አስፈላጊው ግብዓት ቀርቦላቸው ሥራ እንዲጀምሩ ተደርጓል ብለዋል።

የጸጥታ መደፍረሱን የፈጠረው ኃይልም ከበርካታ ቦታዎች ላይ እንዲወጣና ያሰበው ነገር እንዳይሳካ መደረጉን ጠቅሰው፤ የክልሉን ሰላም በዘላቂነት ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት እየተሠራ ነው፤ ሕዝቡ ከሠራዊቱ ጎን ሆኖ በክልሉ ሰላም ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት እያገዘ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ የመንግሥት ሠራተኞችና መምህራን ወደ መደበኛ ሥራቸው ተመልሰው አገልግሎት እንዲሰጡ በተሠራው ሥራ በግንባር ቀደምነት ወደ ሥራቸው ተመልሰው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። በቀጣይነትም ህብረተሰቡን በማስተባበር ክልሉን ወደ ዘላቂ ሰላም ለመመለስ የሚሠሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ።

ጦርነት አውዳሚ በመሆኑ በጦርነት የሚያተርፍ ኃይል እንደሌለ ያስታወሱት ቢሮ ኃላፊው፤ የሰላም መደፍረስ ሲያጋጥም መላው ህብረተሰብ በተለይ ሴቶች፣ ህጻናትና አቅመ ደካሞች ይበልጥ ተጎጂዎች ይሆናሉ። በመሆኑም የትኛውም ጥያቄና ሃሳብ አለኝ የሚል አካል ሁሉ ጥያቄውን ወደጠረጴዛ በማምጣት በሰላማዊ ትግል ሕዝብ የሚፈልገውን እንዲመርጥ እድል መፍጠር ያስፈልጋል ብለዋል።

# ሀገራዊ ምክክሩ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በሚል ርዕሰ ጉዳይ ለሚዲያ ባለሙያዎችና አመራሮች በአዳማ ከተማ ሥልጠና ተሰጥቷል።

በመርሀ ግብሩ ላይ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ዋና ኮሚሽነር መስፍን ዓርአያ (ፐ/ር) እንደተናገሩት፤ መገናኛ ብዙሃን የሀገራዊ ምክክር አስፈላጊነትና ዓላማና ለሀገር የሚያገኘውን ሁለተናዊ ጥቅም በመረዳት በሁሉም ቋንቋዎች ተደራሽ በማድረግ ረገድ የማይተካ ሚናቸውን በጉልህ ሊወጡ ይገባል።

ለሀገራዊ ምክክር ስኬታማነት መገናኛ ብዙሃን ትልቅ ሀገራዊ ሃላፊነት አለባቸው ያሉት ዋና ኮሚሽነሩ፤ በተለይ ሀገራዊ ምክክሩ አስፈላጊነት ዓላማውንና ሥራዎቹን በተመለከተ ህብረተሰቡ በበቂ መንገድ እንዲረዳ ማድረግ ይገባል ሲሉ ጠቁመዋል።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ በበኩላቸው፤ ሀገራዊ ምክክር በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማምጣትና የጋራ መግባባት ለመፍጠር አስፈላጊነቱ አይጠያይቅም፤ ይህን ሀገራዊ ዓላማ ለማሳካትና የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት መገናኛ ብዙሃን ግንባር ቀደም ሚና አላቸው ብለዋል።

ችግሮቻችንን በውይይት ለመፍታት በሚደረገው ጥረት መገናኛ ብዙሃን መረጃዎችን ለህዝብ በተገቢው መንገድ በማቅረብ ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም መልዕክት አስተላልፈዋል።

ኮሚሽኑ ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የጀመረውን አበረታች ጅምር አጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ እስካሁን ላደረጉት ሥራም ምስጋና ይገባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ እውነቱ አለነ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አካታችነት የሀገራዊ ምክክር መርሆ ነው።

በኢትዮጵያ በኃይል ዘላቂ ሰላምንና መግባባትን ለማምጣት ብዙ ተሞክሯል ነገር ግን አተልሳካም ያሉት አቶ እውነቱ፤ ከዚህ መነሻነት ችግሮችን በምክክር መፍታቱ ተመራጭ አማራጭ በመሆኑ መገናኛ ብዙሃን ሰላማዊውን መንገድ በመከተል በይበልጥ ሊሠሩ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ኮሚሽኑ ውጣ ውረዶችንም ቢያልፍም ያለምንም ጣልቃ ገብነት የሀገራዊ ምክክር ሥራዎችን ለመሥራት በርካታ ተግባራትን ማከናወኑ የሚበረታታ መሆኑን ጠቁመው፤ የሀገራዊ ምክክር ዓላማዎች ስኬታማ እንዲሆኑ መገናኛ ብዙሃን የማይተካ ሚናቸውን መወጣት ከቻሉ የተሻለ መግባባትን መፍጠር እንደሚቻል ተናግረዋል።

የመገናኛ ብዙሃን እስከአሁን ላደረጉት ሥራ ምስጋና ቢገባቸውም ቀሪ ሥራዎች ስላሉ ጠንክሮ መሥራት ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የሚዲያ መሪዎች በበኩላቸው፤ የተጀመረውን የሀገራዊ ምክክር ሒደት ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ አሠራሮችን በመቀየስ ወደ ሥራ መግባታቸውን ገልፀዋል።

የኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ግዛቸው ገቢሳ፤ ተቋማቸው በ18 ቋንቋዎች አማካኝነት የተለያዩ መረጃዎችን ተደራሽ እያደረጉ መሆኑን አስታውቀው፤ የምክክር ሒደቱ የሁላችንንም ተሳትፎ ስለሚጠይቅ አጠንክረን እንቀጥላለን ብለዋል።

የፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አድማሱ ዳምጠው በበኩላቸው፤ የሀገራዊ ምክክር ሥራውን ይበልጥ ለመደገፍ አዳዲስ ይዘቶችን በመጨመር በቁርጠኝነት እየሠራን ይገኛል ሲሉ ሃሳብ ሰጥተዋል።

የአሀዱ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ጥበቡ በለጠ በበኩላቸው፤ የሀገር ሰላምና የዜጎች የዕርስ በርስ ትስስር እንዲጠናከር እየሠሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በሥልጠናው ሀገራዊ ምክክር ጽንሰ ሃሳብ፣ የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮዎች፣ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በሕግ ለማቋቋም ያስገደዱ ምክንያቶችና የምክክር ሂደቱ አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ ገለጻ ተደርጓል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## የሰገሌ ጦርነት

**ዋለልኝ አየለ**

በኢትዮጵያ ውስጥ ከተደረጉ የጦርነት ታሪኮች ውስጥ የሰገሌ ጦርነት አንዱ ነው። በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ከ107 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም የተደረገውን የሰገሌ ጦርነት ዘርዘር አድርገን እናስታውሳለን።

በሌላ በኩል ደግሞ ባለፈው ሐሙስ የተከበረውን የመከላከያ ቀን ምክንያት በማድረግ ከ116 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 15 ቀን 1900 የተመሰረተውን የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ የመከላከያ ሚኒስቴር (በያኔው አጠራር የጦር ሚኒስቴር) እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው በዚህ ሳምንት የተከናወኑ ሌሎች ዓለም አቀፍ እና የአገር ውስጥ ታሪኮችን እናስታውስ።

ከ91 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 13 ቀን 1925 ዓ.ም ታላቁ ሠዓሊ እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ተወለዱ።

ከ78 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 14 ቀን 1938 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (United Nations) በይፋ ተመስርቶ ስራ ጀመረ (ቻርተሩ በስራ ላይ መዋል መጀመሩ ተበሰረ)። ከቅኝ ገዢ ኃይሎች ነፃ የነበረችው ኢትዮጵያም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መስራች ነበረችና በወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው የተመራው የልዑካን ቡድን ሰኔ 19 ቀን 1937 ዓ.ም ሳን ፍራንሲስኮ ከተማ ላይ፣ በሳን ፍራንሲስኮ የጦር መታሰቢያና ኪነ ጥበብ ማዕከል ውስጥ የድርጅቱን የቃል ኪዳን ሰነድ (የመመስረቻ ስምምነት/Charter) ፈረመ።

ከ50 ዓመታት በፊት ጥቅምት 15 ቀን 1966 ዓ.ም ሻምበል አበበ ቢቂላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

ከ116 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 15 ቀን 1900 ዓ.ም ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የመከላከያ ሚኒስቴር (የጦር ሚኒስቴር) መሥሪያ ቤትን አቋቋመች። ይህን መነሻ በማድረግ በየዓመቱ ጥቅምት 15 ቀን ‹‹የሠራዊቱ ቀን›› ሆኖ እንዲከበር ተወስኗል። እነሆ ዘንድሮም የመከላከያ ቀን ‹‹ለ116ኛ ጊዜ›› ተብሎ እየተከበረ ነው። የዘንድሮው በዜና ሽፋን ስለሚዘረዘር ከ116 ዓመታት በፊት የነበረውን ሁነት እናስታውስ።

የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንደሚሉት፤ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ‹‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል›› የሚል አመለካከት አልነበራቸውም። ለመንግሥት ድርጅታዊ መሰረትና ቀጣይነት ለመስጠት በ1900 ዓ.ም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን አቋቋሙ። እንደ ፕሮፌሰሩ ገለጻ፤ የመጀመሪያዎቹ ሚኒስትሮች አዲስ አውሮፓዊ ካባ የለበሱ የቤተ መንግሥት ባለሟሎች ናቸው። ይህም የዳግማዊ አጼ ምኒልክን ባሕል እና ዘመናዊ ሥልጣኔን የማስታረቅ ፍላጎት ነው።

የጦር ሚኒስቴር ዋና ተግባር የነበረው የጦር ሥልጠና መስጠት ሲሆን፤ የመጀመሪያው የጦር ሚኒስትር ፊትአውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ናቸው።

ከ112 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 17 ቀን 1904 ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በአርበኝነት ተጋድሎ ዘመን የማይሽረው አኩሪ ገድል ከፈፀሙት ኢትዮጵያውያን አርበኞች መካከል አንዷ የሆኑት ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ከበደች ስዩም ተወለዱ።

አሁን በዝርዝር የምናየውን የሰገሌ ጦርነት እናስታውስ። ከ107 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም፤ መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ ሚካኤል በሸዋ መኳንንትና ኢትዮጵያን ለመቀራመት አሰፍስፈው ይጠብቁ በነበሩ የውጭ ኃይሎች ሴራ ከአልጋ ወራሽነታቸው ከተሻሩ በኋላ፣ አባታቸው ንጉሥ ሚካኤል አሊ የልጃቸውን ስልጣን ለማስመለስ ባደረጉት ጥረት፣ ከማዕከላዊ መንግሥቱ ጦር ጋር የመጨረሻውን ጦርነት፣ ሰገሌ ላይ፣ አደረጉ።

የሰገሌ ጦርነት በሥልጣን ሽኩቻ ከተደረጉ የእርስበርስ ጦርነቶች ሁሉ በአስከፊነቱ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው። ከዛሬ 107 ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ምን ያህል ይሆን ነበር? የሚለውን ታሳቢ እናድርግና 16 ሺህ ያህል ሰዎች የተጨፋጨፉበት ጦርነት ነው።

የሰገሌ ጦርነት መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ ሚካኤል በመኳንንቱና ኢትዮጵያን ለመቀራመት አሰፍስፈው ይጠብቁ በነበሩ ቄሳራውያን (እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ እና ጣሊያን) ኃይሎች ሴራ ከአልጋ ወራሽነታቸው ከተሻሩ በኋላ፣ አባታቸው ንጉሥ ሚካኤል አሊ የልጃቸውን ስልጣን ለማስመለስ ከማዕከላዊ መንግሥቱ ጦር ጋር የመጨረሻውን ጦርነት ያደረጉበት ነው።

**ከ116 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 15 ቀን 1900 ዓ.ም ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የመከላከያ ሚኒስቴር (የጦር ሚኒስቴር) መሥሪያ ቤትን አቋቋመች። ይህን መነሻ በማድረግ በየዓመቱ ጥቅምት 15 ቀን ‹‹የሠራዊቱ ቀን›› ሆኖ እንዲከበር ተወስኗል**

በ1906 ዓ.ም በልጃቸው አማካኝነት ‹‹የወሎ፣ የትግሬና የጎጃም ንጉሥ›› ተብለው የተሾሙት ንጉሥ ሚካኤል አሊ፣ በ1909 ዓ.ም የልጃቸውን ከዙፋን መሻር ሲሰሙ ‹‹ቢያጠፋ እንኳ እኔ እመክርና አርመው የነበረውን ልጄን እንዴት ሳያማክሩኝ የአባቱን ዙፋን ያስለቅቁታል?›› በማለት ‹‹የጠፋ ልጄን አፋልጉኝ›› ብለው 80 ሺህ ወታደሮቻቸውን አስከትለው ወደ ሸዋ ዘመቱ።

የንጉሥ ሚካኤልን ጦር ለመግጠም በማዕከላዊው መንግሥት በኩል 120 ሺህ ጦር ተዘጋጅቶ የመጀመሪያው ጦርነት ከዋናው ጦርነት ቀደም ብሎ ጥቅምት 7 ቀን 1909 ዓ.ም በደብረ ብርሃንና አንኮበር መካከል በሚገኘው ቶራ መስክ ላይ ተካሄደ።

በቶራ መስክ ጦርነትም የንጉሥ ሚካኤል ጦር አሸነፈ። በዚህ ውጊያ ላይ የሸዋው የጦር መሪ ራስ ልዑልሰገድ አጥናፍሰገድን ጨምሮ በርካታ የጦር አዛዦችና ወታደሮች አለቁ። ለጦርነቱ 120 ሺህ ጦር ይዘጋጅ እንጂ ከዚህ መካከል ቁጥሩ በርከት ያለው የሸዋ ጦር ከንጉሥ ሚካኤል ጦር ጋር የተዋጋው ሰገሌ ላይ ነበር።

ከድሉ በኋላም፤ የጦር ሚኒስትሩና የማዕከላዊው መንግሥት ቁልፍ ሰው የነበሩት ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ (አባ መላ) ገፀ በረከትና ላይ ላዩን ሲያዩት እርቅ ውስጥ ውስጡን ደግሞ ማዘናጊያ የመሰለ ቃላት በመላክ የወሎው ጌታና ጦራቸው ተዘናግተው እንዲቆዩ አደረጉ። ‹‹በሰላም መወያቱ ይሻላል›› የሚል ሃሳብ ያለውና ውሉ ያልለየውን ቃል የሰሙት ንጉሥ ሚካኤልም የመጀመሪያው ድላቸውን እንደጨበጡ ሰገሌ ሜዳ ላይ ሰፍረው ቆዩ።

ከቶራ መስኩ ጦርነት 10 ቀናት በኋላ ዋናውን ጦርነት ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም የንጉሥ ሚካኤል ጦርና የማዕከላዊው መንግሥት ጦር ሰገሌ በተባለው ሜዳማ ስፍራ ላይ ከባድ ጦርነት አካሄዱ። የማዕከላዊው መንግሥት ቁልፍ ሰው በነበሩት በጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ እቅድ አውጪነትና መሪነት ለቀናት ያህል በስውር ከበባ ሲያደርግ የቆየው የማዕከላዊው መንግሥት ጦር የወሎን ጦር ባላሰበው



መንገድ አጠቃው።

በዚህ ጦርነት ላይ የጦር ሰራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ ሆነው የዘመቱት ራስ ተፈሪ መኮንን ሲሆኑ ከእርሳቸው ጋርም ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ እና ራስ ካሳ ኃይሉ መሪ ሆነው ተሳትፈዋል። በውጊያውም የንጉሥ ሚካኤል ጦር ያለቀው አልቆ የተረፈው ሲበታተን ንጉሥ ሚካኤልም ተማረኩ። የሰገሌው ጦርነት ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ብዙ ሰው ያለቀበት ከባዱ ውጊያ እንደነበር በታሪክ ተመዝግቧል።

ንጉሥ ሚካኤል በሰገሌው ጦርነት ተሸንፈው፣ ተማርከው አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ሲያልፉ ክብራቸው ተዋርዶ እንደነበር የታሪክ ጸሐፍት አስፍረውታል።

‹‹ሐበሻና የሰገሌው አብዮት›› የሚለውን መፅሐፍ የፃፈው እንግሊዛዊ ጸሐፊ በበኩሉ‹‹ …ንጉሥ ሚካኤል ሀገሪቱ አሉኝ ከምትላቸው ጀግና የግዛት አስተዳዳሪዎችና የጦር መሪዎች አንዱ ነበሩ … ያ ከንቱ ልጅ ከክብራቸው ዝቅ እንዲሉ አደረጋቸው…›› በማለት ጽፏል።

በእርግጥ የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ እንግሊዛዊ በመሆኑና እንግሊዝ ከማዕከላዊው መንግሥት ሹማምንት ጋር በማሴር ልጅ ኢያሱ ከዙፋናቸው እንዲሻሩ ትልቁን ድርሻ የተወጣች ቄሳራዊ ኃይል ስለሆነች ፀሐፊው እንደዚያ ብለው ቢጽፉ የሚገርም አይደለም፤ በመጽሐፉ ውስጥ በርካታ የተዛቡ ታሪኮች አሉ የሚል ወቀሳም ሲቀርብበት ነበር።

‹‹ተፈሪ መኮንን፡ ረጅሙ የስልጣን ጉዞ›› በሚለው የክቡር አምባሳደር ዘውዴ ረታ መጽሐፍ ላይም ስለ ጦርነቱና ከውጊያው በኋላ ስለተፈፀሙት ድርጊቶች ተብራርቷል።

በሰገሌው ጦርነት ላይ የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት እንዳለ የተለያዩ የታሪክ ጸሐፊዎች ጽፈዋል። ልጅ ኢያሱ መፈንቅለ መንግሥት እንዲደረግባቸው አድርገዋል። በነገራችን ላይ እርሳቸው በቀጥታ ‹‹መፈንቅለ መንግሥት›› ባይሉትም ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ‹‹ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ›› በሚለው መጽሐፋቸው መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም በልጅ ኢያሱ ላይ የተደረገውን አድማ በገደምዳሜው ገልጸውታል። ካህናቱና መኳንንቱ ከዚህ በኋላ ልጅ ኢያሱን አውርደን የአጼ ምኒልክን ልጅ ዘውዲቱን አንግሰናል ማለታቸውን ራሳቸው አጼ ኃይለሥላሴ ጽፈዋል።

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ከአድዋ ድል በኋላ የቆዩባቸው አስር ዓመታት (ከ1888 ዓ.ም እስከ 1898 ዓ.ም) የሰላምና የመረጋጋት ወቅት እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። ንጉሡ ታመው አልጋ ላይ ሳሉ የሥልጣን ሽኩቻ እንዳያገረሽ በማሰብ መላ ዘየዱ። በወቅቱ በጎረቤት አገራት የቅኝ ግዛት ይዘው የነበሩት እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን በለንደን የሦስትዮሽ ውል ተፈራርመው ‹‹እርስዎ ድንገት ቢያርፉ አገር እንዳትበጠበጥ ሦስታችን መንግሥታት የበላይ ጠባቂ ሆነን አገር ለማረጋጋት…›› የሚል ይዘት ያለው ደብዳቤ ለምኒልክ ይልካሉ።

ንጉሡም አገሪቱን ለጅቦች አሳልፎ ላለመስጠት ለሦስቱ አገራት ቅኝ ገዥዎች በማያሻማ መልክ ግልፅ ያለ መልዕክት አስተላለፉ። « እኔ ብሞት ኢትዮጵያ በአልጋ ወራሼ አማካይነት ትቀጥላለች፤ የተረጋጋ ሥርዓትም እናቆማለንና አታስቡ » ካሉ በኋላ እርምጃዎችን ወሰዱ።

በወቅቱ ንጉሥ ምኒልክ ሲሞቱ በይፋ ያልተገለጸበት ምክንያትም የአገር ውስጥ የሥልጣን ሽኩቻ ይቀሰቀሳል፤ በጎረቤት አገሮች ያሉ ያደፈጡት ቅኝ ገዥዎችም አደጋ እንዳይደቅኑ በመስጋት ሊሆን እንደሚችል ሰነዶች ያስረዳሉ።

በወቅቱ በ1900 ዓ.ም በሀገሪቱ የመጀመሪያውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት አቋቋሙ። ከወሎው ኢማም መሀመድ አሊ (ራስ ሚካኤል) የተወለደው የልጅ ልጃቸው ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሻቸው መሆኑን አወጁ።

ልጅ እያሱ ገና ልጅ ስለነበሩም የሸዋው ራስ ተሰማ ናደውን የልጅ ኢያሱ ሞግዚት አድርገው ሰየሙ። ራስ ተሰማ ሲሞቱ ሌላ ሞግዚት ለመሰየም እየተከናወነ ባለው ተግባር በመኳንንቱ ዘንድ እኔ እሆን እኔ እሆን የሚል ነገር ተከሰተ፤ ሁኔታው ያላማራቸው ልጅ እያሱ በሸዋ ሞግዚት አያስፈልገኝም ወደሚል ድምዳሜ ደረሱ። ይህ የሚሆነው አጼ ምኒልክ ታመው በነበሩበት ወቅት ነው።

ልጅ ኢያሱ በአስተዳደር ቆይታቸው በጠረፍ አካባቢዎች የሚያደርጉት ተደጋጋሚ ጉብኝት በመኳንንቱ ዘንድ አልተወደደም።

በአገር ውስጥ ከሃይማኖት ጋር ጭምር የተያያዘ ሽኩቻ ሲነዛ በውጭ ደግሞ፤ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ከእንግሊዝ ፈረንሳይና ጣሊያን በተፃራሪ ደረጃ ለነበሩት ጀርመንና ቱርክ ድጋፋቸውን አሳይተዋል በሚልም በሌሎቹ ነጮች ዘንድ ጥርስ ተነከሰባቸው፤ በአገር ውስጥም አድማ ተጠነሰሰባቸው።

በእነዚህ ምክንያቶች በልጅ ኢያሱ መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ከሥልጣን ተሽረው (መፈንቅለ መንግሥት) ዘውዲቱ ምኒልክ ንግሥት እና ተፈሪ መኮንን ደግሞ አልጋ ወራሽ መሆናቸው ይፋ ተደረገ።

ይህኔ ነው የልጅ ኢያሱ አባት ጦራቸውን አዝምተው ከማዕከላዊው መንግሥት ጋር በተደረገ ጦርነት ያ ሁሉ ደም አፋሳሽ እልቂት የተከሰተው።

እንግዲህ ከዚህ ምን እንማራለን ከተባለ፤ የውጭ ሴራ ከድሮም ጀምሮ የነበረ መሆኑን እና የውስጥ የሥልጣን ሽኩቻ ድሮም የነበረ መሆኑ ነው። የሥልጣን ፍላጎት እንጂ የዘር አለመሆኑን ነው። ምክንያቱም የተላለቀው የአንድ አካባቢ ሕዝብ ነው። ልጅ ኢያሱ የአጼ ምኒልክ የልጅ ልጅ ነው። ዘውዲቱ የአጼ ምኒልክ ልጅ ናት። ስለዚህ ኢያሱን ገልብጦ ዘውዲቱን ማንገስ ከሥልጣን ፍላጎት ውጭ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

ከመቶ ምናምን ዓመታት በፊት የነበሩ የታሪክ ክስቶችን የምናስታውሰው ዛሬ ዓለም የሥልጣኔ ማማ ላይ ባለበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ሆነን ነው። ስለዚህ ዘመኑን የሚመጥን አስተሳሰብ ይኑረን እና ታሪክን እንዲህ በታሪክነቱ ብቻ የምናስታውሰው እንሁን!

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

# ጭር ሲል የማይወደው ሠዓሊ

**ቤዛ እሸቱ**

የዘወትር ትራንስፖርቱ የኤሌክትሪክ ሞተር ነው። ግን ሞተሩን በአዲስነቱ ከገበያ አልገዛውም። ከቀድሞ ባለቤቱ ጋር እያለ ከፍተኛ አደጋ ደርሶበት ከጥቅም ውጭ መሆኑን ብዙዎች ተስማምተውበታል። የኤሌክትሪክ ሞተሩ ነብስ ዘርቶ ያገለግላል ብሎ ያልጠበቀው የቀድሞ ባለቤትም ለሠዓሊ ሰለሞን ከበደ በሰባት ሺህ ብር ሸጠለት። ለእድሳቱ መኪና የሚገዛ ብር አውጥቼበታለሁ ቢልም ሞተሩን ለመጠገን የሄደበት ርቀት ርካታ እንደሚሰጠው ይናገራል። አብዛኛው እቃ በሀገር ውስጥ ስለማገይገኝ ከውጭ እያዘዘ በርካታ ጊዜም ወጪ አድርጎበታል።

በኤሌክትሪክ ከሚሰራው ሞተር በፊት በኤሌክትሪክ የሚሰራ ስኩተር ነበረው። ብስክሌት ከከተማ አልፎ በየመልካምድሩ መንዳት ዋና መዝናኛው ነው። ግን ከሥሙ በፊት ማዕረግ የሆነው፤ እንዲሁም መተዳደሪያው ሥዕል ነው። ሠዓሊ ሰለሞን ከበደ ውልደቱ አዲስ አበባ ሰሜን ማዘጋጃ ነው። በቤታቸው አራት ናቸው፤ እናትና አባቱ እሱና ታናሽ እህቱ። እድለኛ ሆነን ዘመናችን ቆንጆ ነበር የሚለው ሠዓሊው በዘመኑ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ውስን ስለነበሩ አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፈው ነገሮችን በመቆራረጥ፣ በመፍጠር እንዲሁም ብዙ እንቅስቃሴ ያላቸውን ጨዋታዎች በመጫወት መሆኑን ያስታውሳል። ለቡሄ ከቆርኪና ከዱላ መሳሪያ አዘጋጅቶ ሆያ ሆዬ ጨፍሮ፤ ለእንቁጣጣሽ አበባ ሥሎ ወዳጅ ቤተሰብን እንኳን አደረሳችሁ ብሎ ልጅነቱን በደንብ ኖሮታል።

ጥበብ እድገት የሕዝብ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን የተከታተለበት ነው። ከዘጠነኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ትምህርቱን ድል በትግል ትምህርት ቤት ተከታትሏል። በትምህርቱም የተሻለ ውጤት የሚያመጣ ጎበዝ ተማሪ ነበር። ለዛም ይሆናል ወላጆቹ በሚሰራቸው ሥዕሎች እየተደነቁ ከማበረታታት ውጪ አጥና፣ ጊዜህን አታባክንና መሰል በብዙ የኪነጥበብ ፈላጊ ልጆች ቤት የሚሰሙ ጭቅጭቆች እነሱ ቤት አልነበሩም። ሥዕል ይወዳል፤ ለዚህም ለሥዕል ትምህርትም ለየት ያለ ትኩረት ያደርጋል።

ሆኖም እሱ በተማረባቸው ትምህርት ቤቶች አብዛኛውን ጊዜ በሥዕል መምህርነት የሚመደቡት መምህራን በቋሚነት የሌላ ትምህርት መምህራን የሆኑና ሥዕል ሙያቸው ባይሆንም በተደራቢነት ማስተማር ይገደዱ ነበር። ሆኖም እድለኛ ሲሆን ጥበብ እድገት የሕዝብ ትምህርት ቤት እየተማረ ሳለ ሥዕል ሙያው የሆነ መምህር ገጠመው። ያኔ ሥዕልን የተማረ በዘርፉ እውቀት ያለው መምህር ሲገጥመው የተሻለ ድጋፍ ነበረው። በትምህርት ቤት ውስጥ የሥነ-ጥበብ ክበብ ነበረ፤ በዛም ተሳታፊ ነበር።

“ቤተሰቦቼ በምሰራው ነገር ደስተኞች ነበሩ፤ ለዚህ ያበቃኝም የነሱ ድጋፍ ነው።” የሚለው ሠዓሊው፤ የልጅነት ጨዋታዎች ቢስቡትም ባገኘው አጋጣሚ ሥዕል መሣል መለያው ነበር። የመጀመሪያው ቆንጆ ሥራዬ በማለት የሚያስታውሰው የአምስተኛ ክፍል ተማሪ እያለ በበላው የአቡወለድ ብስኩት ካርቶን ላይ የሣለውን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሥል ነው። በወቅቱ እናቱ በልጇ ሥራ በመደሰቷ ለሰፈር ሰው እየዞረች “እዩት ልጄ የሳለውን” በማለት ማሳየቷ ይበልጥ ሞራል እንደሆነው ያስታውሳል።

በትምህርት ቤት ቆይታው ከመሰሎቹ ጋር የትምህርት ቤታቸውን ግድግዳ ያስውባሉ። ከዚህ በተጨማሪ ደብተሩ ገለጦ ሲደረግ በሚመለከቱት አስደናቂ ሥዕል የሚገረሙ ሰዎች አንተማ ሠዓሊ ነው የምትሆነው እያሉ የወደፊቱን ተነበዩለት። ያኔ እሱም ሠዓሊ መሆን እንዳለበት ተረዳ። የሰውም ማበረታታት እሱም በውስጡ ያለው ችሎታና ፍላጎት ተደምሮ 12 እንደጨረሰ በቀጥታ አለ ፈለገ ሰላም የሥነ-ጥበብ ትምህርት ቤትን ተቀላቀለ። በትምህርት ቤቱ የነበረውን ቆይታ ነጻነት የተሞላበትና ስለጥበብ ለማሰብ ብዙ ጊዜ የሚገኝበት፤ አስፈላጊው ድጋፍ ስለሚገኝ እምቅ አቅምና ተሰጥኦን ለማውጣት የሚቻልበት ጊዜ በማለት ያስታውሰዋል። የአራት ዓመቱን ትምህርተ አጠናቆ በ2001 ዓ.ም በፔይንቲንግ በዲግሪ በጥሩ ውጤት ተመርቋል።




በአለፈለገሰላም ተማሪ እያለ ያስበው የነበረውና ከተመረቀ በኋላ የገጠመው ነገር አልገጥም ብሎት ትንሽ ተቸግሮ ነበር። ተማሪ ሳለ ያስብ የነበረው ትምህርቱን እንደጨረሰ የራሱን ስቱዲዮ ከፍቶ ሥዕል መሳልን ብቻ ነበር። እናም እንደተመረቀ አደረገው። የተወሰነ ጊዜ የሙሉ ጊዜ የስቱዲዮ ሠዓሊ በመሆን ኑሮን ታግሏል። ግን ሲያየው በባዶ ኪስ ሥም ያልተከለ ጀማሪ ሠዓሊ ሆኖ የሙሉ ጊዜ የስቱዲዮ ሠዓሊ መሆን ሊያወላዳው አልቻለም። የስቱዲዮ ወጪን ለመሸፈንም ሆነ ለስዕሉ አስፈላጊ የሆኑትን ቀለምና መሰል ግብዓት ለማሟላት ገንዘብ የግድ ያስፈልግ ነበር። ቀለሞቹ ደግሞ ከውጭ የሚመጡ ስለሆነ ዋጋቸው ወደድ ይላል። ቀለሞቹን ለመግዛት ሥዕል መሳያውን ሸራ ለማዘጋጀት እንዲሁም የዕለት ወጪን ለመሸፈን ገንዘብ ያስፈልጋል። ይሄን ለማሟላት ግዴታ ገቢ እንደሚያስፈልገው ሲረዳ በአንድ የግል ትምህርት ቤት ማስተማር ጀመረ።

ሠዓሊ ሰለሞን ሰዓቱን አብቃቅቶ በመምህርነትና በስቱዲዮ ሠዓሊነት ላይ ተሰማራ። ያኔ የተማረውን ሥዕል በትምህርት ቤቶች ለልጆች ያስተምራል፤ በሚቀረው ጊዜ ሥዕሉን ይስላል። በማስተማር ከሚያገኘው ገቢ እየቀነሰ ለሥዕሉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማሟላት ጀመረ። በዚህ ሁኔታ ሥዕሉን እየሸጠ ገቢ ማግኘት ሲጀምር ከሚያስተምርበት ሰዓት እየቀነሰ አብዛኛውን ጊዜ ለሥዕል ሥራ መስጠት ጀመረ። በሂደት በሥራው እየዳበረ በሥዕል አድናቂዎች ዘንድም ሥሙን እያኖረ ሲሄድ ኑሮም ሥራም ቀለለው።

ሠዓሊው በግሉ ሦስት ኤግዚቢሽኖችን አሳይቷል። በግሩፕ ከሌሎች ሰዓሊያን ጋር በመሆን በርካታ ኤግዚብሽኖች ላይ ሥራውን አሳይቷል። በዓመት አንዴ በሂልተን ሆቴል በሚዘጋጀው “ቢግ አርት ሴል“ ላይ በቋሚነት ሥራዎቹን ያቀርባል። በኃልፍ ክለብ፣ በመኮንኖች ክበብ በሚዘጋጁ የአርት ኤግዚቢሽኖች ላይ ይሳተፋል። በሚዘጋጁ የሥዕል ውድድሮች ላይ ይሳተፋል። በቅርቡ በፈረንሳይ ኤምባሲ አዘጋጅነት በተካሄደው ግንብ ላይ በሚሰራ ሥዕል (ስትሬት አርት) ውድድር ላይ ተካፍሎ አራተኛ በመውጣቱ አሌያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የሥዕል ኤግዚቢሽን የማሳየት እድል አግኝቷል። አንድ ወር በቆየው ኤግዚቢሽንም በርካታ ሥራዎቹን የመሸጥ እድል አግኝቷል።

ለሥዕሎቼ ብዙ ጊዜ ዋጋ አላወጣም የሚለው ሰዓሊው፣ ሰው ሥራዬን ወዶት አቅም ስለሌለው ብቻ እንዳይገዛው አላደርግም ይላል። ሥዕሉን የወደደው ሰው ገንዘብ ከሌለው እሱ አለኝ ብሎ የሚጠራው ዋጋ የሥራውን ክብር የማይቀንስ ከሆነ እንደሚስማማ ይናገራል። በትናንሽ ሳይዝ (30 በ30) የሚሰሩት ስዕሎች ከስምንት ሺህ ብር አንስቶ መጠናቸው ከፍ ያሉት እስከ 80ሺ. ብር ይሸጣሉ። ሥዕልን ሸራ ላይ ከመሳል በተጨማሪ ሆቴሎችን ካፌዎችንና መኖሪያ ቤቶችን በደንበኞቹ ፍላጎት የማስዋብ አገልግሎት ይሰጣል። የሥዕል ሥራው መደበኛ ገገር የሆኑ ሰዎች የወደዱትን ሥዕል ወስደው በሂደት ክፍያ የሚፈጽሙበት ሁኔታ መኖሩን ይናገራል።

አርጅተው ጥቅም እንዳይሰጡ ተደርገው የተጣሉ ነገሮችን በመሰብሰብ ድጋሚ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ የሶል መለያው ነው። ሞተር ሳይክል ብስክሌት የሚወዳቸው ነገሮች ናቸው። ከጥቅም ውጭ የሆኑ ሞተሮችን በመሰብሰብ ሙሉ የውጭ ገጽታቸውም ሆነ የውስጥ አካላቸው አድሶ ሙሉ ግልጋሎት እንዲሰጡ ያደርጋል። “አድቬንቸር ደስ ይለኛል” የሚለው ሰዓሊው





ያነሳሳኛልም ይላል፤ ብስክሌት የሚወደውም ለዛ መሆኑን ይናገራል።

በብስክሌቱ የማይዳስሰው መልካምድር የለም። ተራራ፣ ጫካ፣ ሜዳ ሸንተረሩን በብስክሌት ያቆራርጣል። መጀመሪያ አካባቢ ብስክሌቱና እሱ ነበሩ የሸርሸሩ አካላት። ከቆይታ በኋላ አዲስ አበባ ማውንቴን ባይከርስ ግሩፕ የተሰኘ የሱ መሰል በብስክሌት ከከተማ ወጣ የማለት ፍላጎት ያላቸውን አባላት ሲያገኝ ተቀላቅሎ አብረው ጉዞ ማድረግ ጀመሩ። በጋራ መሆኑ ረዥም ጉዞ ለመጓዝ እንደሚያስችልና እሱም ከግሩፑ አባላት ጋር በመሆን ከአዲስ አበባ ሐዋሳ፣ ወንጪ ድረስ መጓዛቸውን ያስታውሳል። ጉዞ በሚያደርጉበት ሰዓት የተለያዩ በዓሎችንና ማሕበረሰቦች በቅርበት ማየት ይቻላል። ይሄ ለሠዓሊ አሪፍ ግብዓት እንደሚሆን በመጥቀስ እሱም በጉዞው ፎቶ እንደሚያነሳና በተጓዘበት አካባቢ ከሚኖሩ ማሕበረሰቦች ጋር ሲያወራ በርካታ ነገሮችን እንደሚያገኝና ለሥዕል ሥራው ጥሩ ግብዓት መሆኑን ይናገራል።

ሶል ለሥዕል ሥራው የሚሆን ተመስጦ የሚያገኘው ከግርግር ነው። እንደሌሎች የኪነጥበብ ሰዎች “ዛሬ” መታለችና ዝም በሉልኝ፤ ብቻዬን ተውኝ ይሉት ነገር እሱ ጋ ቦታ የለውም። በራሱ ቃል እንዲያውም “ጭር ሲል አልወድም” በማለት ይገልጸዋል። መኖሪያ ቤቱ ውስጥ በሚገኘው ስቱዲዮ ሲሰራ ጓደኞቹ መተው ቡና ተፈልቶ እየተጠጣና እየተጫወቱ እንደሚሰራ ይናገራል። እሱና ስኬች ቡኩ አይነጣጠሉም። በሄደበት አብሯው ትጓዛለች፤ እናም የሀሳብ መምጫው አይታወቅምና በሄደበት ሀሳብ ከመጣለት እዛው ይነድፋል። ዘመኑ የማሕበራዊ ሚድያ ነውና እሱም ዘመን ያመጣቸው ማሕበራዊ የትስስር ገጾች አሉት። በዛ ላይ ሥራዎቹን ይለቃል፤ የወደዳቸው እነሱን ስለመግዛትም ሆኖ ሌላ ስለማሳል በማሕበራዊ ሚድያ ያናግሩታል።

ከትዳር አጋሩ ወይዘሮ ጣዕሞ ብርሀኑ ጋር ከተጣመረ ሁለት ዓመት ሞላው። በቅርቡ ደግሞ የሴት ልጅ አባት ሆኗል። አብዛኛው ሥራዬን የሚገዙት ለጉብኝት የሚመጡ የውጭ ሀገር ዜጎች ናቸው የሚለው ሠዓሊው ሰለሞን፤ ሥራውን በቋሚነት ለማኩሻ አርት ጋለሪ እንደሚያስረክብ ይናገራል። በጋለሪው ሥራቸው በኮሚሽን የሚሸጥ ሲሆን አብዛኛው ገገር ቀጥታ ከሰዓሊው ጋር አይገናኝም። ሆኖም ስዕሉን በጣም የወደዱት ሸማቾች ሰዓሊውን ማግኘት እንፈልጋለን እያሉ እንደሚያገኙት ይናገራል። ከዛ ውጭ በኤግዚብሽንና በቀጥታ እሱን በማግኘት የሚገዙትን ካልሆነ በጋለሪ የሚገዙት አብዛኛው የሥዕሉ ገዥዎችን ማንነት እንደማያውቅ ይናገራል። ከገቢያቸው ቆጥበው፣ አልሞላ ሲል ተበድረው ሥዕሉን የሚገዙ ኢትዮጵያውያን ደንበኞቹም በርካቶች ናቸው።

በገበያ ላይ ለመቆየት በተቻለ አቅም ሰዓሊው ባገኘው አጋጣሚ ተጠቅሞ ሥዕል እንደሚስል ራሱን ማሳወቅ አለበት። እኔ የማውቃቸው ጎበዝ ሰዓሊዎች ሆነው ዘግተው የተቀመጡ ሰዓሊዎች አሉ የሚለው ሠዓሊው፤ ሰው የግድ ስለሠዓሊው ማወቅ አለበት ይላል። ስለሠዓሊው ማንነት ምን እንደሚሰራ መታወቅ አለበት። በሀገራችን ገበያ የማፈላለግ ገዥዎችን የማፈላለግ (የኔትዎርኪንግና የማርኬቲንግ) ሥራ ባለሙያው ራሱ መስራት ይጠበቅበታል። በውጭው ዓለም ጋለሪዎች እንዲሁም ሥዕል ሰብሳቢዎች አፈላልገው ቤቱ ድረስ የሚመጡ መሆኑን በመጥቀስ በሀገራችን የግድ ሠዓሊው መንቀሳቀስ እንደሚጠበቅበት ያነሳል።

ስዕል ከጀመረ ቶሎ አይነሳም፤ ለዚህም ይመስላል አብዛኞቹ ሥዕሎቹን በቶሎ ያጠናቅቃል። ለዚህም አብዛኞቹ ሥዕሎች ቢበዛ በሦስት ቀናት ይጠናቀቃሉ። ሆኖም እስከ ሦስት ወራት የወሰዱበት ሥራዎችም አሉት። አብዛኞቹ ስዕሎቹ ተፈጥሮና (ኔቸር) መልካ ከተማ (ሲቲ ስኬፐ) ላይ ያተኮሩ ናቸው። የሚስልበት የአሳሳል ዘይቤ “ኢምፐሬሽኒዝም” ይሰኛል። የሱ ስዕሎች ትክክለኛውን ነገር አስመስሎ መሳል ሳይሆን የስዕሉን ስሜት ማምጣት ላይ ያተኮረ ነው። በአብዛኛው በተለይ ለትልልቅ ስዕሎቹ አክለሪክ ቀለም ምርጫው ነው። አክለሪክ ቶሎ የሚደርቅ የቀለም አይነት በመሆኑ ይበልጥ እንዲጠቀመው ምክንያት ሆኗል። የሥዕሎቹ መጠን አነስተኛ ሲሆንና ለቀጣ የሚፈልጉ ስዕሎች ሲሆኑ የዘይት ቀለም ይጠቀማል። የዘይት ቀለም ለመድረቅ እስከ አንድ ወር ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ ብዙም ምርጫው አይደለም።

“አልሸጣቸውም፤ የግል ስብስቦቼ ናቸው” ብሎ ለሚያስቀራቸው ሥዕሎች ርዕስ ይሰጣል። ለገበያ የሚያወጣቸው ሥዕሎች ላይ ርዕስ ከመሰየም ይቆጠባል። ተመልካች የፈለገውን እንዲሰይም ሙሉ ነጻነት ይሰጣል። ለተመልካች ርዕስ ማስቀመጥ ይገድባል ብሎ ስለሚያስብ ተመልካች የመረጠውን ርዕስ እንዲሰይምና እንዲተረጉም ነጻነት መስጠትን ይመርጣል። ሥዕል መሣልም፣ ማስቀመጥም ይወዳል። ለዚህም ይመስላል ከ35 በላይ የራሱን ሥዕሎች የማይሸጡ ብሎ ወስኖ ለይቷቸዋል። ሆኖም ከዚህ ቀደም አንድ የሥዕል ገገር ቀድሞ የገዛቸውን ሥዕሎቹን የያዘበት መንገድ ስለገረመው አይሸጡም ብሎ ከለያቸው ሥዕሎቹ መሃል አንዱን በነጻ፣ በስጦታ አበርክቶለታል። ቤት ውስጥ ያስቀመጣቸውን ሥራዎቹን ሲያይ ለሌላም ሥራ እንደሚያነሳሱት ይናገራል።

“አድቬንቸር እወዳለሁ” የሚለው ሰዓሊው ለዚህም ሳይከሉ እንደሚረዳውና የተበላሹ የተባሉ ነገሮችን ጠግኖ ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስደስተው መሆኑን ይናገራል። በተለይ እሁድ ቀን መርካቶ ከሚገኘው ምናለሽ ተራ አይጠፋም። ምናለሽ ተራ አይሰሩም ተብለው የተጣሉ እቃዎች በብዛት ለገበያ ይቀርባሉ። ከገበያው ላይ ቀልቡን የሳቡትን እቃዎች ሸምቶ ይመለሳል። ከዛ እነሱን በፈርጅ በፈርጁ “እንዴት ቢሆኑ ይሻላል?" ብሎ ማሰብና እነሱን መጠገን ጊዜ ሰጥቶ የሚሰራው መዝናኛው ነው። “በዚ መልክ የምሰራቸውን እቃዎች አልሸጣቸውም፤ አስቀምጣቸዋለሁ” የሚለው ሠዓሊው፤ ነገር ግን ለራሱ ከመጠገን ባለፈ ይሄን ችሎታውን የሚያውቁ ሰዎች የድሮ እቃ ሲበላሽባቸው እንዲጠግንላቸው ያመጡለታል። እሱም እንደነበረ አድርጎ መጠገኑን ተክኖበታል።

ከልጅነቱ አንስቶ መፍቻ ይዞ መታገል የወደቀን እቃ ለመጠገን መጣር መታወቂያው ነበር። በዚህም ልምድ ትምህርት ቤት ሆኖለታል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በዩቲዩብ ቪድዮዎችን በማየት እራሱን ማስተማሩ የበለጠ አግዞታል። ምግብ አልመርጥም ያገኘሁትን እበላለሁ የሚለው ሠዓሊው፤ ሆኖም ከምግብ አትክልትና ፍራፍሬ አይሰለቸኝም ይላል።

አዳዲስ ነገር መሞከር ያስደስተዋል፤ ከሙከራዎቹ ውስጥ በካሴት ክር ላይ የሰራቸው የበርካታ ታዋቂ ሰዎች ምሥሎች ይገኙሉ። የካሴት ምርጫው በካሴት ሙዚቃ እየሰማ ከማደጉ ጋር ይገናኛል። ቤት ውስጥ አባቱ ሙዚቃ ይወድ ስለነበር በርካታ ካሴት እንደነበር ያስታውሳል። ሲያድግ ካሴት እየነካ፣ እንዲሁም እየሰማ በማደጉ በይበልጥ በዘመኑ ይሰማቸው የነበሩትን ከ50 በላይ ድምጻውያንና የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾችን የካሴት ክርን በማጣበቅ ምሥላቸውን በማስፈር አስታውሷቸዋል። በቀጣይ ከሀገር ተሻግሮ ሥራዎቹን ማሳየትን ያልማል፤ እኛም ይህ ውጥኑ ይሰምርለት ዘንድ በመመኘት አበቃን።

# ዓለም አቀፍ

## ደቡብ አፍሪካ ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት የማይልኩ ወላጆች ልታስር ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የደቡብ አፍሪካ ፓርላማ ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት የማይልኩ ወላጆችን ወህኒ ቤት እንዲወርዱ የሚፈቅድ ሕግ አረቀቀ።

ደቡብ አፍሪካ ያረቀቀችው አዲሱ የትምህርት ሕግ አንድ ተማሪ ትምህርት ቢያቋርጥ ወይም ተማሪው ዕድሜው ለትምህርት ደርሶ ትምህርት ቤት ካልገባ ወላጆች እስከ 12 ወራት በእስር እንዲቀጡ ያዛል።

ይህ አዲሱ ሕግ በትምህርት ቤቶች አካላዊ ቅጣቶችንም ይከለክላል። ረቂቅ ሕጉ በአገሪቱ ፓርላማ አባላት በ223 ድጋፍ እና 83 ተቃውሞ ጸድቋል።

ደቡብ አፍሪካን እያስተዳደረው የሚገኘው አፍሪካን ናሽናል ኮንግረስ (ኤኤንሲ) ፓርቲ "ሕጉ አሁናዊ እና ታሪካዊ ፈተናዎችን በመሻር የትምህርት ስርዓቱን ያዘምናል" ብሏል።

ዋነኛ ተቃዋሚ ፓርቲ ዴሞክራቲክ አሊያንስ ግን ፓርላማው ያጸደቀውን ሕግ ተችቷል። የዘፈቀደ እስር ሊያጋጥም እንደሚችል ስጋታቸውን የገለጹ ደቡብ አፍሪካውያንም አሉ።

እንደ ፓርቲው ከሆነ ይህ የሕግ አዋጅ መንግሥት በትምህርት ቤቶች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር እንዲኖሩት አድርጎ የትምህርት ስርዓት እንዲወድቅ ሊያደርግ ይችላል ሲል ስጋቱን ገልጿል።

የትምህርት ባለሙያዎች የደቡብ አፍሪካ የትምህርት ስርዓት ቀውስ ውስጥ ነው ያለው ይላሉ። በደቡብ አፍሪካ ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎች ቁጥር ትንሽ የሚባል አይደለም።

የአገሪቱ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በ2022 ባወጣው አሃዝ ላይ ዕድሜያቸው 15 ዓመት ከሆናቸው ተማሪዎች ሶስት በመቶ እንዲሁም ዕድሜያቸው 17 ከሆኑ ዘጠኝ በመቶ ያክሉ እ.አ.አ. 2021 ላይ ትምህርት አቋርጠዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ሪዲንግ ሊትረሲ ስተዲ ዓለም አቀፍ ተቋም በሰራው ጥናት ለማንበብ የሚቸገሩ በርካታ ተማሪዎች ከሚገኙባቸው አገራት መካከል አንዷ ደቡብ አፍሪካ መሆኗን አሳይቶ ነበር።



በዚህ ዓመት የተደረገ ጥናት ዕድሜያቸው 10 ከሆኑ 10 ደቡብ አፍሪካውያን ተማሪዎች ስምንት ያክሉ ለማንበብ እንደሚቸገሩ የሀገሪቷ የትምህርት ዘርፍ ጥናት ያመለክታል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## የቀድሞ የዩኬ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን በጋዜጠኝነት ተቀጠሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቀድሞው የዩናይትድ ኪንግደም ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን በጋዜጠኝነት ተቀጠሩ። ጂቢ ኒውስ በተባለው የቴሌቪዥን ጣቢያ ነው የተቀጠሩት።

ጆንሰን በቴሌቪዥን ጣቢያው የፕሮግራም አቅራቢ፣ አዘጋጅና ተንታኝ ይሆናሉ። በቀጣይ ዓመት የአሜሪካና የዩኬ ምርጫ በመዘገብ "ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ" ተብሏል።

"የእንግሊዝን ኃይል የሚያሳይ መሰናዶ" ያቀርባሉም ብሏል ጂኒ ኒውስ። በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩች ምልከታቸውን ለማጋራት ቃል ገብተዋል።

በዴይሊ ሜይል ላይም አምደኛ የሆኑት ቦሪስ ጆንሰን ሥራቸውን በአውሮፓውያኑ አዲስ ዓመት ይጀምራሉ። ቦሪስ ጆንሰን በኤክስ ገጻቸው ላይ "ጂቢ ኒውስን እንደምቀላቀል ስነግራችሁ በደስታ ነው" ብለው ቪድዮ አጋርተዋል።

"በሩሲያ፣ ቻይና፣ ዩክሬንና ሌሎችም ጉዳዮች እውነተኛ ዕይታዬን አቀርባለሁ" ብለዋል። "እንግሊዝ በዓለም ስላላት ዕምቅ አቅምና ፈተናዎቻችንም እናገራለሁ" ሲሉ አክለዋል።

ቦሪስ ከሥልጣን እንዲወርዱ ከፍተኛ ጫና መፈጠሩን ተከትሎ ነው አምና የወረዱት። በኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ወቅት ያሳዩት አመራር አሁንም ምርመራ እየተደረገበት ነው።

በዩኬ የቀድሞ መሪዎች ሥልጣን በለቀቁ በሁለት ዓመታት ስለሚይዙት ሥራ የሚያማክሩት አገራዊ ኮሚቴ አለ። ይህ ኮሚቴ ቦሪስ ጆንሰን ጂቢ ኒውስ መግባታቸው ከመንግሥት መርህ ጋር የሚጻረር ስላልሆነ ፈቅዷል።

ሥልጣን ላይ ሳሉ ያገኟቸውን መረጃዎች ያለአግባብ እንዳይጠቀሙ መርሆች ተቀምጠዋል። በተጨማሪም ጂቢ ኒውስን ወክለው መንግሥት ላይ ጫና እንዳያደርጉም ጥንቃቄ ይደረጋል።

ይህ የሚሆነው ሥልጣን ከለቀቁበት ጊዜ በኋላ ላሉት ሁለት ዓመታት ነው። ቦሪስ ከሥልጣን በለቀቁ በአምስት ወራት ውስጥ በተለያዩ መሰናዶዎች ንግግር በማድረግና የግል የሕይወት ታሪካቸውን ለመጻፍ በመስማማት አራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ፓውንድ አግኝተዋል።

ጂቢ ኒውስ ከዚህ በፊት ታዋቂው ኮሜድያን ጆን ክሊስን ቀጥሯል። ጣቢያው ቦሪስ ጆንሰንን ከቀጠረ በኋላ የተመልካቾቹ ቁጥር ከፍ እንደሚል ይጠበቃል።



ቦሪስ ጆንሰን


### በድጋሚ የወጣ ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

የሆለታ ንብ ምርምር ማዕከል በስሩ ላሉት ተሽከርካሪዎች የመለዋወጫ እቃዎችን ራሱ ገዝቶ በማቅረብ ጋራጆች የሚጠግኑበትን የእጅ ዋጋ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለአንድ ዓመት ተሽከርካሪዎቹን ለማስጠገን ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ የሚከተሉትን የጨረታ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ተጫራቾችን እንዲወዳደሩ ይጋብዛል፡፡

1. የብቃት ማረጋገጫ ያላቸው፣
2. ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸው፣ ቫት የተመዘገቡና የዘመኑን ግብር የከፈሉበት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
3. ለተሽከርካሪዎቹ ጥበቃና ደህንነት በቂ የማቆሚያ ግቢ ያላቸው፣
4. በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፀውን የጨረታ ማስከበሪያ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ (CPO) በሆለታ ንብ ምርምር ማዕከል ስም ማስያዝ አለባቸው፡፡
5. አሸናፊ ተጫራቾች ውል ሲፈራረሙ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና 10% ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር ) ብቻ በመክፈል ከመስሪያ ቤቱ ቢሮ ቁጥር 6 መግዛት ይችላሉ፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ አንድ ዋናና ኮፒውን በሰም በታሸገ ኤንቬሎፕ በማቅረብ እስከ 16ኛው ቀን ድረስ ለዚሁ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ የጨረታው ሳጥን በዚሁ ቀን ጠዋት 3፡30 ተዘግቶ በ4፡00 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ እለቱ በአል ወይም ዝግ ከሆነ በቀጣዩ የስራ ቀን ጨረታው ይከፈታል፡፡ ለተሸነፉት ተጫራቾች ያስያዙት ገንዘብ ወዲያውኑ ይመለስላቸዋል፡፡
8. ማንኛውም ተጫራች በሌላው ተጫራች ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይችልም፡፡
9. የተቀየሩ አሮጌ የመለዋወጫ እቃዎች ለመ/ቤቱ ተመላሽ ይደረጋሉ፡፡፡
10. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡-** ወልመራ ወረዳ ሆለታ ከተማ ከአዲስ አበባ በአምቦ መስመር በ30 ኪ.ሜ. ላይ ይገኛል፡፡

**ስልክ ቁጥር** 011-237-0350 /011-237-0023

**የሆለታ ንብ ምርምር ማዕከል**

### የጨረታ ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የቃሊቲ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለ2016 ዓ.ም የሚከተሉትን የተለያዩ ዕቃዎች በግልፅ ጨረታ ቁጥር 01/2016 አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ የሠራተኞች የደንብ ልብስ፣ አላቂ የቢሮ ዕቃዎችና የፅህፈት መሳሪያዎች፣ የፅዳት ዕቃዎች ፣ አላቂ የትምህርት ዕቃዎች፤ የስፖርት ትጥቅና ልዩልዩ ግብአቶች ናቸው፡፡ በዚህ ጨረታ ላይ መሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባችኋል፡፡

1. በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣
2. የዘመኑን ግብር የከፈሉና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
3. በአቅራቢነት ለመመዝገባቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
4. የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ተመዝጋቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
5. የቲን ተመዝጋቢ የሆኑና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ

- ተጫራቾች የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል ቢሮ ቁ.3(ፋይናንስ ቢሮ) የጨረታ ሰነድ መውሰድ ይችላሉ፡፡
- ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች ጨረታ ከመከፈቻው ቀን በፊት ኦርጅናልና ደረጃውን የጠበቁ ናሙናዎች ለት/ቤቱ ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ (bid bond) ብር 5000.00(አምስት ሺ ብር) ሲፒኦ በማሰራት ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዘው ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ በገዙት ሰነድ ላይ የዋጋ ማቅረቢያ ቦታ በግልፅ ከቫት ጭምር ያለውን ዋጋ ድምሩን ጨምሮ ሙሉ በሙሉ በመሙላት በመጨረሻ ቦታ ላይ ፊርማና የድርጅታቸውን ማህተም በማሳረፍ ኦርጅናልና ኮፒ ሰነድ ለያይቶ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማሸግ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዘወትር በስራ ሠዓት ከ2፡30 እስከ 11፡00 ድረስ ቢሮ ቁ.3 በመቅረብ ለዚህ ጨረታ በተዘጋጀው በሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባችኋል፡፡
- ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ11ኛው የስራ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሠዓት ይከፈታል፡፡ የተጫራቾች ወይም የህጋዊ ወኪሎቻቸው አለመገኘት የጨረታውን መክፈት አያስተጓጉልም፡፡
- የጨረታ አሸናፊዎቹ ተለይተው ከተገለፁበት ቀነ ገደብ ቀጥሎ ባለው ተከታታይ 7 የስራ ቀናት ውስጥ አሸናፊዎች የውል ማስከበሪያ 10% በማስያዝ ውል መፈፀም አለባቸው፡፡ ላላሸነፉ ተጫራቾች ደግሞ ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ መውሰድ ይችላሉ፡፡
- አሸናፊዎቹ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው (በተጫራቹ) ትራንስፖርት ቃሊቲ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ድረስ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

መስሪያ ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብት አለው፡፡

**አድራሻ፡-** አዲስ አበባ፣ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ከቃሊቲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አለፍ ብሎ ቸራሊያ ሳይደርስ በስተግራ በኩል 150 ሜትር ያህል ገባ ብሎ የሚገኘው የቃሊቲ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር፡-** 011-439-6550/011-4394857

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የቃሊቲ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት**

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

## በኦሮሚያ ክልል - ስልማት የተመረጡ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ስፍራዎች

**ዳግም ከበደ**






> የቱሪዝም ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን በቀዳሚነት "ሰላም" እና የተረጋጋ ከባቢ ከምንም በላይ ሊኖር ይገባል። በተለይ የግል ባለሀብቶች በነፃነትና ሀብታቸውና ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ ኢንቨስትመንት ላይ እንዲሳተፉ "ሰላም ቁልፍ ሚና ይጫወታል

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መንግስት ለቱሪዝም ዘርፍ የሰጠውን ልዩ ትኩረት ተከትሎ መነቃቃቶች እየታዩ ናቸው። በመዳረሻ ልማት ግንባታ፣ በገበያና ማስተዋወቅ እንዲሁም አዳዲስ የመስህብ ስፍራዎች ተጨማሪ የዘርፉን አቅም እንዲገነቡ ከማድረግ አንስቶ ልዩ ልዩ ለውጦች እየተደረጉ ናቸው። በተለይ ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የተጠናቀቁና የጎብኝዎች ምርጫን ያሰፉ መዳረሻዎችን እዚህ ላይ እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል። በተለያዩ ክልሎች በመጨረሻው የግንባታ ምዕራፍ ላይ የሚገኙ ትላልቅ የቱሪዝም ፕሮጀክቶችም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለዘርፉ የተሰጠውን ልዩ ትኩረት የሚያሳዩና የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን ያነቃቁ እንደሆኑ ይታመናል።

የቱሪዝም ዘርፍ በኢኮኖሚ ላይ በጎ ተፅዕኖ እንዲኖረውና ለእድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት በቀጣይም በመንግስት በርካታ ተግባራት እንዲከናወኑ ይጠበቃል። ከእነዚህ ውስጥ ጠንካራ ፖሊሲ፣ ሕግና ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ማውጣትና ተግባር ላይ ማዋል የሚሉት ይገኙባቸዋል። ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ እንዲሁም ሕጎች ተግባራዊ እንዲሆኑ መደላድል ከመፍጠር በተጨማሪ የግሉ ዘርፍ በቱሪዝም ላይ የሚኖረው የበለጠ ተሳትፎ እንዲጎለብት መንገድ መጥረግም የመንግስት ኃላፊነት ነው።

ቱሪዝም የመዳረሻ ልማት (መሰረተ ልማት)፣ የገበያና ማስተዋወቅ ተግባር በጥልቀት ሊሰራባቸው ከሚገቡ ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው። በተለይ ኢትዮጵያ በዘርፉ ያላትን ሀብት በማስተዋወቅ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ማስፋፋትና የግሉን ዘርፍ ማሳተፍ የአስፈፃሚው ድርሻ ነው። በዘርፉ መዋለንዋይ በማፍሰስ የሚሳተፉ ባለሀብቶች እና የግል ተቋማትን መጋበዝ እና ትኩረታቸውን መሳብ ይገባል።

ከዚህ አንፃር ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በመንግስት በኩል ተግባራዊ የተደረጉ ስራዎች አሉ። በግሉ አቅም የማይሸፈኑ የመዳረሻ መሰረተ ልማት ግንባታዎችን በመስራት ኢንቨስተሮችን የመስዕብ ስፍራ ባሉባቸው ቦታዎች ሆቴሎች፣ ሎጆችና ልዩ ልዩ የአገልግሎት ተቋማትን እንዲገነቡና የሆስፒታሊቲ ንኡስ ዘርፍ እንዲጎለብት ጥረት መደረጉን መረጃዎች ያሳያሉ። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆኑት የገበታ ለሸገር፣ ገበታ ለሀገርና ገበታ ለትውልድ የተሰኙት ፕሮጀክቶች ናቸው።

የቱሪዝም ዘርፉ የሚፈለገውን ትኩረት እንዲያገኝና የግል ባለሀብቶችም በኢንቨስትመንት ተሳታፊ እንዲሆኑ የፌደራል መንግስትና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚያከናውናቸው ተግባሮች ባሻገር የክልል መንግስታት በሚያስተዳድሩት ክልል ውስጥ ያሉ የመስህብ ሀብቶችን በማስተዋወቅና በማልማት የድርሻቸውን ይወጣሉ። ኢንቨስተሮችም በቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎች ላይ በልዩ ልዩ አገልግሎት እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ጥረ ያደርጋሉ።

የግል ባለሀብቶች በቱሪዝም ኢንቨስትመንት በስፋት ከሚሳተፉባቸው ክልሎች ውስጥም የሲዳማ፣ የቀድሞው የደቡብ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች፣ የአማራና የኦሮሚያና ክልሎች ቀዳሚ ተጠቃሽ ናቸው። በእነዚህ ክልሎች በርካታ የቱሪዝም መስህቦች ከመኖራቸውም ባሻገር የአገር ውስጥና የውጪ ቱሪስት ፍሰቱም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመብራት፣ የመንገድ እና የመሳሰሉትን መሰረተ ልማት ፍላጎቶች በማሟላት ኢንቨስተሮች በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ላይ እንዲሰማሩ ማበረታቻዎች እየተደረጉ ነው። ባለሀብቶችም በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ዘርፉን የሚያነቃቁ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተሳታፊ ለመሆን ፍላጎት እያሳዩ ነው።

በያዝነው ዓመት በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ላይ ከባለሀብቶች ጋር በቅርበት ለመስራት እቅድ ነድፈው ከሚንቀሳቀሱ ክልሎች መካከል የኦሮሚያ ክልል አንዱ ነው። ክልሉ መስከረም ወር ላይ የዓለም የቱሪዝምን ቀን በማስመልከት ባዘጋጀው "የቱሪዝም ሳምንት አውደ ርዕይ" ላይ ይህንን እቅዱን ይፋ አድርጓል። በተለይ ኢንቨስተሮች ሊያለሟቸው የሚችሉና አዳዲስ የሆኑ ስምንት መዳረሻዎችን ለይቶ የማስተዋወቅ ስራ መጀመሩን አስታውቋል። ይህንን በተመለከተ በኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን የሀብት ማሰባሰብና የቱሪዝም ፈንድ ዳይሬክተር የሆነው አቶ ሂክሰን ደበሌ እንደሚሉት፤ ከዚህ ቀደም በቱሪዝም ዘርፍ ያለው ተነሳሽነትና መነቃቃት ደካማ ነበር። ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ውስጥ መንግስት ዘርፉን ዋንኛው የኢኮኖሚ ምሰሶ በማድረግ የወሰዳቸው የማስተካከያ እርምጃዎች መሻሻሎች እንዲታዩ ምክንያት ሆነዋል።

ከተቋቋመ ሶስት ዓመታትን እያስቆጠረ የሚገኘው የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽንም ይህንን ለውጥ ለመደገፍ እየሰራ መሆኑን አቶ ሂክሰን በመግለፅ በተለይ የክልሉን የመስህብ ስፍራዎች በማስተዋወቅ፣ የኢንቨስትመንት ስፍራዎችን በመለየት እና ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ገቢ በማሳደግ ረገድ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ እንደሆነ ይናገራል።

በኢትዮጵያ በታሪክ፣ በተፈጥሮ፣ በቅርስ በባህል እጅግ በርካታ የሚaሆኑ የቱሪዝም መስህቦች እንዳሉ የሚናገረው አቶ ሂክሰን ከዚህ ውስጥ በርካታ የዘርፉ ሀብት በኦሮሚያ ክልል እንደሚገኝ ይገልፃል። በክልሉ ባሉ አካባቢዎች የተለያየ መልከዓ ምድር፣ ባህል፣ ቅርስ እንዲሁም ልዩ ልዩ የቱሪዝም መስህቦች መኖሩን ጠቅሶ፣ እምቅ ሀብት ቢኖርም ያንን አልምቶ፣ አስተዋውቆና ወደ ኢኮኖሚ ቀይሮ ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ በሚፈለገው ልክ እንዳልተሰራ ይናገራል።

"የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን በቅርብ ጊዜ ውስጥ በክልሉ ወደ 20 የሚደርሱ አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማስተዋወቅ ውጤት እያመጣ ነው" የሚለው ዳይሬክተሩ፣ ኮሚሽኑ ይህንን ስራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ይገልፃል። በአዳዲስ የመዳረሻ ስፍራዎች ላይ የግል ባለሀብቶች ገብተው እንዲያለሙ በትብብር ከክልሉ መንግስት ጋር እንዲሰሩ ፕሮጀክት ተቀርፆ እየተሰራ መሆኑን ጠቁሟል።

የኦሮሚያ ክልል የቆዳ ስፋት ትልቅ መሆኑንና እምቅ የቱሪዝም ሀብት መኖሩን የሚያነሳው ዳይሬክተሩ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉንም መዳረሻዎች ለማልማትና ባለሃብቱን በኢንቨስትመንት እንዲሳተፍ ለማድረግ እንደሚቸግር ይገልፃል። በተለይ በውስን የሰው ኃይል፣ ከጊዜና የመሰረተ ልማትን በሚፈለገው ልክ ለማዳረስ ከሚጠይቀው ሰፊ ሀብት አንፃር በሁሉም አካባቢ መድረስ እንደሚቸግር ይገልፃል። ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ በ2016 ዓ.ም ብቻ በኦሮሚያ ክልል የግል ባለሀብቱ በኢንቨስትመንት ቢሳተፍባቸው ውጤታማ እንደሚሆኑ የታመነባቸው ስምንት ቦታዎችን መለየት እንደተቻለ ይገልፃል። እነዚህን የመስህብ ስፍራዎች ለባለሀብቶች በማስተዋወቅና መዋለንዋይ እንዲያፈሱ ለማሳመን እቅድ በመንደፍ የማስተዋወቅ ስራ እየተሰራ መሆኑን አመልክቷል።

"የመጀመሪያው ባለሀብቱ እንዲሳተፍበት የሚፈለገው እና የማሕበረሰብ አቀፍ ሎጅ እንዲገነባ የታቀደበት የፍል ውሀና ውብ መልከዓ ምድር ያለው 'ሻሎ' የተባለ ስፍራ ነው" የሚለው ዳይሬክተሩ፣ ስፍራውም ወደ ሀዋሳ መስመር ሲኬድ ጥቁር ውሀ እንደሚገኝ ጠቁሟል። ስፍራው በኦሮሚያ ክልል ስር ያለ አዲስ መዳረሻ መሆኑን ይገልፃል። ይህ ስፍራ ኢንቨስተሩ እንዲሳተፍባቸውና እንዲለሙ ከሚፈለጉት ስምንት መዳረሻዎች መካከል አንዱ እንደሆነ ይገልፃል። በስፍራው ባለሀብቱ ቢሳተፍም ማሕበረሰቡንና ወጣቱን ያሳተፈ አካታች የቱሪዝም ኢንቨስትመንት እንዲሆን ታስቦ የማስተዋወቅ ስራ እየተሰራ እንደሆነ አስታውቋል።

በሆቴልና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ በሁለተኛነት የተለየው መዳረሻ የአዳማ ከተማ መሆኑን የሚገልፀው አቶ ሂክሰን ደበሌ፤ በከተማዋ በ "ማይስ ቱሪዝም" (የስብሰባ፣ ኮንፍረንስ እና ኤግዚቢሽን) ዘርፍ በርከት ያሉ ባለሀብቶች መዋለንዋያቸውን እንዲያወጡ እየተሰራ መሆኑን ይገልፃል። ከተማዋ ታላላቅ ስብሰባዎችን፣ አውደ ርዕይ እና ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን በምታከናውንበት ወቅት ያንን መሸከም የሚያስችል የሆቴል፣ የሎጅና መሰል የሆስፒታሊቲ ስፍራዎች በባለሀብቶች እንዲገነቡ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን መስራት መጀመሩን ይገልፃል።

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን በ2016 ዓ.ም የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ባለሀብቶች እንዲገቡበትና እንዲሳተፉ በማሰብ ከለያቸው ስፈራዎች መካከል ሌላው በሰላሌ (ደብረ ሊባኖስ) አካባቢ የሚገኝና "ጫገል" ተብሎ የሚጠራ ስፍራ አንዱ ነው። በዚያ አካባቢ ያለው የፖርቹጊዝ ድልድል፣ የጭላዳ ባቡን ዝርያ፣ የጀማ ፏፏቴን፣ መልከዓ ምድሩን ጨምሮ ልዩ ልዩ መስህቦችን የቱሪስት መዳረሻ እንዲሆኑ እየተሰራ እንደሆነ ይጠቁማል። በዚህ አካባቢ ባለሃብቱ ገንብቶ የአገልግሎት ዘርፉን እንዲያዘምን እና የልማት ስራዎች ላይ እንዲሳተፍ እንደሚፈለግ ይገልፃል።

ዳይሬክተሩ እንዳለው፤ ኮሚሽኑ ከላይ ከተነሱት የተለዩ መስህብ ስፍራዎች በተጨማሪ በአብያታ ሻላ፣ በባሌ፣ በቦረና እና ኢሊባቡር ኢንቨስተሮች ቱሪዝምን መሰረት አድርገው እንዲሳተፉ ፕሮጀክቶች ቀርፆ እየሰራ ይገኛል። በተለይ በኢሊባቡር አካባቢ የቡና ምርት በስፋት ስለሚታወቅና ልማቱም የተስፋፋ በመሆኑ ከእርሱ ጋር የተያያዘ የቱሪዝም መስህብ በኢንቨስተሮች እንዲጀመር ፍላጎት አለ። በተለምዶ አካባቢው ከጅማ ጀምሮ በኢሊባቡር ወለጋ ድረስ የቡና መስመር "coffee root" መሆኑ ስለሚታመን ይህንን መሰረት ያደረገ የተፈጥሮ ሎጆች እንዲገነቡ መስራት ውስጥ ተገብቷል። ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶችም የቡና ሀብት በሚገኝባቸው እነዚህ አካባቢዎች ለጎብኚዎች ምቹ ሎጆችንና መዝናኛ ስፍራዎች እንዲገነቡ ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠረላቸው ነው።

እምቅ የቱሪዝም ሀብትን ወደ ኢኮኖሚ አቅም ለመቀየር ቅድሚያ መሰራት የሚገባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ መሰረተ ልማት መገንባት፣ ማስተዋወቅ እና የግል ባለሀብትን ማሳተፍ ይጠቀሳሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ መስፈርቶች መሟላታቸው ብቻ በቂ አይደለም። የቱሪዝም ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን በቀዳሚነት "ሰላም" እና የተረጋጋ ከባቢ ከምንም በላይ ሊኖር ይገባል። በተለይ የግል ባለሀብቶች በነፃነትና ሀብታቸውና ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ ኢንቨስትመንት ላይ እንዲሳተፉ "ሰላም ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ቱሪዝም በተለይ ደግሞ ኢንቨስትመንት ያለ ሰላም ሊሳካ እንደማይችል የዘርፉ ባለሙያዎችም ይናገራሉ።

ከላይ ካነሳነው አመክንዮ አኳያ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን በፕሮጀክቱ ለይቶ ኢንቨስተሮች እንዲሳተፉበት በጋበዘባቸው መዳረሻዎች በተሳካ መልኩ ውጤታማ ልማት እንዲከናወንባቸው ከሰላም አንፃር ምን ምቹ ሁኔታ እንዳለ የዝግጅት ክፍላችን ለዳይሬክተሩ ጥያቄ አንስቶ ነበር። እርሳቸውም በክልሉ 90 በመቶ በላይ የተረጋጋና ለቱሪዝም ልማት ምቹ የሆነ ሰላም መኖሩን ይገልፃሉ። ይሁን እንጂ በጉዳዩ ላይ "ምንም እንከን የለም" የሚል ድምዳሜ አለመኖሩን ይናገራሉ። በአጠቃላይ በዓለም ላይ ካለው አለመረጋጋት እና በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚፈጠሩ ግጭቶች ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ነገሮች ቢኖሩም ችግሮቹ በመንግስት ልዩ ትኩረት እልባት እያገኙ መሆኑን ተናግረዋል። ኮሚሽኑም የማሕበረሰቡን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ ከቱሪዝም ልማቱም ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆን በማስቻል ከሰላም አንፃር ራሱ ዘብ የሚሆንበት እድል እየተፈጠረ መሆኑን ገልፀዋል። ከዚህ መነሻ በ2016 በባለሀብቶች ተሳትፎ እንዲለሙ የተመረጡ መዳረሻዎች ስኬታማ አፈፃፀም እንዲኖራቸው የተግባር ስራዎች መጀመራቸውን ነግረውናል።




# ልጆች ስለጤና አጠባበቅ...

**እየሩስ ተስፋዬ**

ሠላም ልጆች እንዴት ናችሁ? ልጆች ሀገራችን በርካታ ምሳሌዊ አነጋገር፣ ተረት እና ምሳሌ እንዲሁም የተለያዩ አባባሎች እንዳሏት ታውቃላችሁ አይደል? በእርግጥ ልጆችዬ ዛሬ ስለ አባባሎቻችን እንዲሁም ተረት እና ምሳሌ ልንነግራችሁ አይደለም። ከዚህ ይልቅ የዛሬ ርዕሰ ጉዳያችንን ‹‹ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ›› በሚለው አባባል ለመጀመር ስለወደድኩ ነው። ልጆችዬ የዚህን አባባል ትርጉሙን ታውቁታላችሁ? ለምታውቁት ሳይሆን ለማታውቁት ምን መሰላችሁ? አንድ ሠው ከመታመሙ በፊት አስቀድሞ ቢጠነቀቅ እና ማድረግ ያለበትን ጥንቃቄ ሁሉ ቢያደርግ ራሱን ከበሽታ መከላከል ይቻለዋል እንደማለት ነው። በተጨማሪም በበሽታው ምክንያት ጉዳት እንዳይገጥመው እና እንዳይንገላታ ይረዳዋል ማለት ነው። ልጆችዬ ጠቃሚ ምክር ነው አይደል? ‹‹በሚገባ›› እንዳላችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም።

ልጆችዬ አስተውላችሁ ከሆነ ከሰሞኑን ራሳችሁን ወይም ቤተሰባችሁን፣ ጓደኞቻችሁን ወይም መምህራኖቻችሁን ብቻ በቅርብ የምታውቋቸው ሰዎች ጉንፋን ወይም መሰል ነገር ተይዘው ታመው ተመልክታችሁ ይሆናል። የጤና ሚኒስቴርም ከሰሞኑን በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተስተዋለው የጉንፋንና ኢንፍሉዌንዛ በሽታ እንዳይስፋፋ ሕብረተሰቡ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት መግለጹን ሰምታችኋል ብዬ እገምታለሁ።

ሚኒስቴሩ ከባለድርሻ አካላት ጋር ባደረገው የዳሰሳ ጥናት አዲስ አበባን ጨምሮ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የጉንፋንና ኢንፍሉዌንዛ በሽታ መከሰታቸውን አረጋግጧል። በጤና ሚኒስቴር የኮቪድ 19 ምላሽ ግብረ-ኃይል ዋና አስተባባሪ ዶክተር መብራቱ ማሴቦ እንደተናገሩት ከሆነ፣



ከጥቅምት ወር መጀመሪያ ጀምሮ በአንዳንድ አካባቢዎች የጉንፋንና ኢንፍሉዌንዛ በሽታ ተከስቷል። የጤና ሚኒስቴርና የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በጋራ በመሆን በሁለት ሺህ ያህል ናሙናዎች ላይ ባደረጉት ምርመራም የበሽታውን መከሰት ማረጋገጣቸውንም መገናኛ ብዙኃን መረጃውን ለሕዝብ እንዲደርስ አድርገዋል።

የትንፋሽ አቅም ማነስ፣ የሰውነት መቆረጣጠምና የድካም ስሜቶች ከሕመሙ ምልክቶች መካከል እንደሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ ቫይረሱ ሳምባ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥርበት ደረጃ ሲደርስ ሳል፣ ከፍተኛ የሆነ የትንፋሽ ማጠርና ሌሎች ምልክቶች እንዲስተዋሉ ያደርጋል። ስለዚህም ምልክቶቹ የታየበት ሠው በአፋጣኝ በጤና ተቋማት ሕክምና ማግኘት እንዳለበት የሕክምና በላሙያዎቹ ይመክራሉ። ልጆች በሽታው ሕዝብ በሚበዛባቸው በትምህርት ቤቶች፣ የገበያ ሥፍራዎች፣ የእምነት ቦታዎች በስፋት የመሠራጨት ዕድሉ ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባችኋል። እንዲሁም በከተሞችና ከፍተኛ መቀራረብ ባለባቸው የመኖሪያ ሥፍራዎች ጭምር የመስፋፋት አዝማሚያ ሊኖረው እንደሚችል ስለሚታመን፤ ልጆችም ሆኑ ወላጆች ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

እጅ በመታጠብ፣ አፍና አፍንጫን በመሸፈን በሽታውን በቀላሉ መከላከል እንደሚቻል እና በበሽታው የተያዙ ሰዎች በቂ እረፍት በመውሰድ፣ ፈሳሽና ትኩስ ነገሮች በመጠቀምና ተገቢውን ሕክምና በማግኘት ሥርጭቱ እንዳይስፋፋ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ባለሙያዎቹ መክረዋል። የጤና ባለሙያዎች የሚሰጧቸውን ምክረሃሳቦች በመተግበር፣ በርና መስኮቶችን በመክፈት በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖር በማድረግ መከላከል የሚቻል ሲሆን፤ የኢንፍሌንዛ ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ የመጣ በመሆኑ ወላጆች ልጆቻቸው የሕመም ምልክት ከታየባቸው አስፈላጊውን ሕክምና እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል። በትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ እና ሠዎች በሚበዙባቸው ስፍራዎች በቂ አየር እንዲኖር በማድረግ እና ለተማሪዎች በተከታታይ ግንዛቤ በመፍጠር በሽታው ከሚያደርሰው ሕመም ራስን ብሎም ሌሎችን ለመከላከል ያስችላል።

ልጆችዬ ምንም እንኳን አሁን ላይ በኮቪድ 19 የሚያዙ ሰዎች ቁጥር አናሳ እና የሚያደርሰውም ጉዳት ቀንሷል ቢባልም፤ ኮቪድ በተቀሰቀሰበት ወቅት ይደረግ የነበረውን ጥንቃቄ አሁንም መተግበር ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪም በየመንገዱ ያለው መጥፎ የቱቦ ሽታ እንዲሁም በየመንገዱ የሚጣሉ ቆሻሻዎች ለጉንፋን እና መሰል በሽታ አጋላጭ መሆናቸውን በመረዳት ማስክ አድርጎ መንቀሳቀስም ተገቢ ነው።

ሌላው ደግሞ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ጉንፋን የያዘው ተማሪ ካለ ወደ ሌላ ተማሪ በተለያየ መንገድ ሊተላለፍ እንደሚችል በመገንዘብ፤ ማስክ በማድረግ፣ እጅን በሳሙና ቶሎ ቶሎ በመታጠብ (ሳኒታይዘር በመጠቀም) ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባ ሲሆን፤ ሳል፣ ራስ ምታት እና ሌሎች ምልክቶች ካልጠፉ ግን ቸል ከማለት ይልቅ ለቤተሰብ በማሳወቅ ወደ ሕክምና ጣቢያ ማምራት ያስፈልጋል።

በተለይም በዚህ ዓመት ትምህርት የጀመሩ ሕፃናት እንዲሁም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን የጤና ሁኔታ በመከታተል ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መምከር ብሎም እገዛ ማድረግ ከመምህራን እና ከወላጆች (አሳዳጊዎች) የሚጠበቅ ኃላፊነት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

ስለዚህም ልጆችዬ ታማችሁ ከትምህርታችሁ እንዳትስተጓጎሉ እና በበሽታው ምክንያት ጉዳት እንዳይረስባችሁ አድርጉ የምትባሉትን የጥንቃቄ ምክሮች በመስማት እና በመተግበር ራሳችሁን ከበሽታ እንድትከላከሉ ያስችላችኋል። በሉ ልጆችዬ ለዛሬው በዚህ እናብቃ። ሁሌም እንደምንላችሁ ትምህርታችሁን በሚገባ ተማሩ፣ አጥኑ፣ የግል ንጽህናችሁን ጠብቁ።

# ስፖርት





# አበበ ቢቂላ - ከአትሌቲክስ ባሻገር

**ብርሃን ፈይሳ**

በርካታ የአትሌቲክስ አድናቂዎች ስፖርቱ አንደበት ኖሮት ‹‹በታሪክ ምርጡ አትሌት ማነው?›› ቢባል ኢትዮጵያዊውን ታላቅ አትሌት አበበ ቢቂላን ያስቀድማል ይላሉ። ዘመናትን አልፎ አሁንም ድረስ ስሙ ከገነነበት ያልወረደበት ምክንያትም ማንም ሊደግመው የማይችለው ድንቅ ታሪክ በመጻፉ ነው። ቆፍጣናው ወታደር ከኦሊምፒክ እስከ ፓራሊምፒክ አስደናቂ ገድሎች ያሉት ቢሆንም ጎልቶ የሚጠቀሰው ግን የሩጫ ሕይወቱ ነው። አበበ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ ባለፈው ጥቅምት 15/2016 ሃምሳ ዓመት ሞላው። በዛሬው የስፖርት ማሕደር አምድም የአበበን ሕይወት የቀየረውን ክስተትና ከአትሌቲክስ ባሻገር የነበረውን ሌላኛውን ገጽታ እንዳስሳለን።

አስደንጋጩ የመኪና አደጋ አበበ ቢቂላ ላይ የደረሰው እአአ በ1969 ነበር። በወርሃ የካቲት አንድ ምሽት ቮልስ ዋገን መኪናውን ያሽከረክር የነበረው ታላቁ አትሌት ያልተጠበቀ አደጋ የደረሰበት ስለመሆኑ የዓለም መገናኛ ብዙሃን በዜናዎቻቸው ተቀባበሉት። የአበበን የሕይወት ታሪክ የጻፈው ቲም ጁዳ ስለ አደጋው መንስኤ በርካታ መላምቶች ይነሱ እንጂ በትክክል ሊጠቀስ የሚችል ምክንያት አለመታወቁን ይገልጻል። ድራማዊ በሆነ ሁኔታ ብሄራዊ ጀግናዋን ልታጣ የተቃረበችው ኢትዮጵያ በሃገር ውስጥ ሕክምና ለውጥ ማምጣት የማይቻል በመሆኑ ከጥቂት ቀናት ክትትል በኋላ ወደ እንግሊዝ ሄዶ የተሻለ ሕክምና እንዲያገኝ አፋጣኝ ውሳኔ ላይ ተደረሰ።

እንኳን ተራ ሰው አትሌቶች በቀላሉ የማይደፍሩትን 42 ኪሎ ሜትር ሮጦ ከጨረሰም በኋላ ሳይደክም ተጨማሪ እንቅስቃሴ ሲያደርግ የሚታወቀው የአበበ ቀልጣፋ ሰውነት በወቅቱ መንቀሳቀስ ተስኖት ነበር። ከቀዶ ሕክምና መልስ ማራቶንን በድል ያጠናቀቀው ጀግናው ሰው፣ በዚያ ግለት ባዶ እግሩን በመሮጥ በርካቶች እጃቸውን በአፋቸው እንዲጭኑ ምክንያት የነበረው የአበበ እግር አልታዘዝ ብሎ (ፓራላይዝድ) በመሆኑ ምክንያት ለስምንት ወራት ሆስፒታል ውስጥ በክትትል እንዲቆይ ሆነ። ከጊዜ በኋላም ለሩጫ የተፈጠረ እግሩ ደግሞ መራመድ ባይችልም ለበርካቶች ተምሳሌትና መነሳሳት ምክንያት የሆነው ጠንካራ መንፈሱ ግን አብሮት ነበር። እናም በሆስፒታል ውስጥ ሆኖ በዊልቸር ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በመሳተፍ ራሱን ለተወዳዳሪነት ሊያበቃ ችሏል።

የመጀመሪያውን ውድድሩንም በዚያው በለንደን በተዘጋጀ የአካል ጉዳተኞች ውድድር ላይ በቀስት ውርወራ እና በጠረጴዛ ቴኒስ ስፖርቶች ነበር ያደረገው። በእርግጥም ድልን በድል ላይ ሲደራርብ የኖረውና ኪሎ ሜትሮችን እንደቀላል ሲያቆራርጥ የነበረ ሰው በዊልቸር ተገድቦ ማየቱ ልብን ይሰብራል። ሆኖም ለጉዳቱ እጅ ሳይሰጥ ሕይወቱ የሆነውን ስፖርት በሌላ መልክ ሲከውን መመልከት የጥንካሬውን ልክ የሚያንጸባርቅና በርካቶችን ሊያስተምር የሚችል ነው። ኀበዝ ቀስተኛ የሆነው ጀግናው አትሌት አበበ ከአንድ ዓመት በኋላ ደግሞ ኖርዌይ ላይ በተደረገ ውድድር በቀስት፣ ጠረጴዛ ቴኒስ እንዲሁም በውሾች በሚጎተት ጋሪ የበረዶ ላይ ሃገር አቋራጭ በመሳተፍ በርካቶችን አስደነቀ። በኢትዮጵያ በማይታወቀው የውሾች ጋሪ ጉተታ ውድድር ላይም 16ቱን ተወዳዳሪዎች ድል በመንሳት 1 ሰዓት ከ16 ደቂቃ ከ17 ሰከንድ በማስመዝገብ ሊያጠናቅቅ ችሏል። በኢትዮጵያ ስፖርት ታሪክ ውስጥም በእነዚህ ስፖርቶች በመወዳደር አበበ ምናልባትም ብቸኛው ሰው ነው።

በዚህ ሁኔታ የቀጠለው አበበ እአአ በ1972 በተካሄደው የሙኒክ ኦሊምፒክ በክብር እንግድነት እንዲገኝ በዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ተጋበዘ። በመክፈቻው ስነስርዓት ላይ ሲገኝም አትሌቶች እንዲሁም በስፍራው የተገኙ የስፖርት ቤተሰቦች ታላቅ አክብሮትና ክብር ሊያሳዩት ችለዋል። በወቅቱ የማራቶን ውድድር አሸናፊ የነበረው አሜሪካዊው አትሌት ፍራንክ ሾርተር ድሉን ያከበረው የአበበን እጅ በመጨበጥ ነበር። ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ አልፎ በኢትዮጵያ ባልተለመደ መልክ ለመጀመሪያ ጊዜ በታላቁ የውድድር መድረክ ኦሊምፒክ ተሳትፎ ሃገሩን ያስጠራው ኋላ ላይም በአስከፊ የመኪና አደጋ ዊልቸር ላይ የዋለው አበበ ተገቢው ክብርና ዕውቅና በኦሊምፒክ ከተሰጠው በኋላ በምድር ላይ የነበረው ቆይታ አጭር ነበር።


ታላቁ አትሌት ከአትሌቲክስ ባሻገር በሌሎች ስፖርቶችም የተሳትፎ ታሪክ አለው፣

በቀጣዩ ዓመት የ41ኛ ዓመት ልደት ሻማዎቹን ያጠፋው ጀግና ከመኪና አደጋው ጋር በተያያዘ ከደረሰበት ውስብስብ ጉዳት ጋር በተያያዘ በሰውነቱ ውስጥ ደም መፍሰሱ ሕይወቱ በአጭሩ እንዲቀጭ ምክንያት ሆነ። አደጋውን ካስተናገደ አራት ዓመታት በኋላም በማይቀርበት የሞት እቅፍ አሸለበ። በወቅቱም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ሃዘን ታወጀ፤ ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለስላሴን ጨምሮ 65ሺ ሰዎች በተገኙበት በታላቅ ወታደራዊ አጀብ በቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን እንዲያርፍ ተደረገ። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጀግና እንደመሆኑ በመቃብሩ ላይ የነሐስ ሐውልት ሲደረግ ስሙ ሕያው ነውና በትውልዱ ውስጥ ሰርጾ ይኖር ዘንድ ትምህርት ቤቶች፣ ስታዲየሞችና ሌሎች ተቋማት ተሰየሙለት።